# ኢፕድ አዲስ ዘመን

እሁድ 83 ዓመት ቁጥር 321 ሐምሌ 21 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




## ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በጎፋ ዞን የመሬት መንሸራተት አደጋ የተጎዱ ቤተሰቦችን በስፍራው በመገኘት አጽናኑ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው በጎፋ ዞን የመሬት መንሸራተት አደጋ የተጎዱ ቤተሰቦችን በስፍራው በመገኘት አጽናኑ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እና ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው እስካሁን የ231 ዜጎችን ሕይወት እንደቀጠፈ በተረጋገጠው የጎፋ ዞን የመሬት መንሸራተት አደጋ የተጎዱ ቤተሰቦችና ማኅበረሰብ በአካል ለማፅናናት በስፍራው መገኘታቸውን የጠቅላይ ሚኒስትር

ጠቅላይ ሚኒስትር ...ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የአደጋ ስጋት ያለባቸውን ዜጎች ወደ ተረጋጉ ቦታዎች ለመውሰድ አራት አካባቢዎች ተለይተዋል

- ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች 60 ሚሊዮን ብር የሚገመት የሰብዓዊ ድጋፍ ተደርጓል

ገጽ 4



## "አገልግሎት አሰጣጥን በቴክኖሎጂ በመደገፍ ጊዜና ሀብትን ከብክነት መታደግ ይገባል"

ወርቁ ጋቸና ( ዶ/ር፤ኢ/ር)
- የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- አገልግሎት አሰጣጥና መረጃ አያያዝን በቴክኖሎጂ በመደገፍ የሀገሪቱን ጊዜና ሀብት ከብክነት መታደግ ይገባል ሲሉ የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ወርቁ ጋቸና (ዶ/ር፤ ኢ/ር) ገለጹ።

ወርቁ ጋቸና ( ዶ/ር፤ኢ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድሎች በአግባቡ በመጠቀም

"አገልግሎት አሰጣጥን...ወደ ገጽ 11 ዞሯል



## የጎርጎራ ፕሮጀክት ለሀገር የሀብት ምንጭ መሆን በሚችል መልኩ ተሠርቷል

- ቱሪስቶች ወደ ስፍራው በመሄድ እየጎበኙት ነው

ገጽ 11



















ዜና

# አምስት ሚሊዮን ዜጎችን የንፁሕ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዷል

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- በ2017 በጀት ዓመት ከአምስት ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያውያንን የንፁሕ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ለማድረግ መታቀዱን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ኢንጅነር ሃብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በ2017 በጀት ዓመት አጠቃላይ የመጠጥ ውሃ ተጠቃሚ የሆነ ሕዝብ ብዛትን ከነበረበት 74 ሚሊዮን 661 ሺህ 037 ወደ 80 ሚሊዮን ለማሳደግ ታቅዷል። በዚህም ከአምስት ሚሊዮን በላይ ዜጎች የንፁሕ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ለማድረግ በትኩረት ይሠራል።

በ2017 በጀት ዓመት አጠቃላይ የመጠጥ ውሃ ተጠቃሚ የሆነ የገጠር ሕዝብ ብዛትን ከነበረበት 54 ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ወደ 64 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ለማሳደግ ታቅዷል ያሉት ኢንጅነር ሃብታሙ (ዶ/ር)፤



በ2016 በጀት ዓመት ሁለት ነጥብ አራት ሚሊዮን የኅብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ በማድረግ አጠቃላይ የገጠር መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ሕዝብ ብዛትን ከነበረበት 52 ነጥብ አራት ሚሊዮን ወደ 54 ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ማሳደግ ተችሏል ብለዋል።

በ2017 በጀት ዓመት አጠቃላይ የመጠጥ ውሃ ተጠቃሚ የሆነ የከተማ ሕዝብ ብዛትን ከነበረበት 19 ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ወደ 20 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ለማሳደግ መታቀዱንም ገልጸዋል።

እንደ ኢንጅነር ሃብታሙ (ዶ/ር) ገለፃ፤ ሀገራዊ የገጠርና የከተማ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን በስታንዳርድ ደረጃ ከነበረበት 69 ነጥብ አምስት በመቶ ወደ 78 ነጥብ ሁለት በመቶ ለማሳደግ ይሠራል። የገጠር መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን በስታንዳርድ አገልግሎት ደረጃ ከነበረበት 66 ነጥብ ሁለት በመቶ ወደ 77 ነጥብ አምስት በመቶ ለማሳደግ ታቅዷል።

የከተማ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን በስታንዳርድ አገልግሎት ደረጃ ከነበረበት 79 በመቶ ወደ 80 በመቶ ለማሳደግ እንደሚሠራም ገልጸዋል።

# ለሁለት ሚሊዮን ዜጎች ነፃ የበጎ ፍቃድ የጤና አገልግሎት ይሰጣል

ማሕሌት ብዙነህ

አዲስ አበባ ፡- በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሁለት ወራት በሚሰጠው የክረምት ሕክምና በጎ ፍቃድ አገልግሎት ለሁለት ሚሊዮን ዜጎች ነፃ የጤና አገልግሎት እንደሚሰጥ የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በሀገር አቀፍ ደረጃ "በጎነት ለጤናችን" በሚል መሪ ቃል የሚካሄደው ነፃ የጤና ምክር፣ ምርመራና ሕክምና አገልግሎት በቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ እና በኤካ ኮተቤ አጠቃላይ ሆስፒታል በትናንትናው እለት ተጀምሯል።

በመድረኩ ላይ የጤና ሚኒስቴር ዶክተር መቅደስ ዳባ እንደገለፁት፤ ለሁለት ወራት በሚቆየው የክረምት ሕክምና በጎ ፍቃድ አገልግሎት ለሁለት ሚሊዮን ዜጎች ነፃ የጤና አገልግሎት ይሰጣል። ከዚህም 75 በመቶ የሚሆነው በክልል ጤና ቢሮዎች ለመስጠት ታቅዷል።

በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅና በኤካ ኮተቤ አጠቃላይ ሆስፒታል የተጀመረው የነፃ ሕክምና በጎ ፍቃድ አገልግሎት ለ7 ቀናት የሚሰጥ መሆኑን ገልጸው፡፡ በዚህም 100 ሺህ ዜጎችን ተጠቃሚ ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል።


በበጎ ፈቃድ የጤና አገልግሎቱ የጤና ምርመራ፣ የምክርና የሕክምና አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑን ገልጸው፣ ማንኛውም ሰው በምርመራ ማዕከሉ በመገኘት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደሚችል ተናግረዋል።

በበጎ ፍቃድ አገልግሎቱ ከነፃ ሕክምና በተጨማሪ በደም ልገሳ 40ሺህ ዩኒት ደም ለመሰብሰብ፣ ለ500 ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ ለማድረግ፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ 15 ዜጎች መኖሪያ ቤት ግንባታና እድሳት ለማካሄድ እና፣ የቆሻሻ ተከላ ለማድረግ መታቀዱንም አብራርተዋል ።

ባለፉት ዓመታት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከክልል ጤና ቢሮዎችና ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር 325 ሰዎችን ተጠቃሚ ያደረጉ 65 መኖሪያ ቤት ግንባታ፣ 11 ሚሊዮን ችግኝ ተከላ፣ አንድ ሺህ 600 ተማሪዎች የተሟላ የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ እንዲሁም ለሦስት ሚሊዮን ዜጎች የነፃ ጤና ምርመራ እና 43 ሺህ ዩኒት የደም ልገሳ መደረጉን አስታውሰዋል። ይህ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በቀጣይ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ሚኒስትሯ ገልፀዋል።

የኤካ ኮተቤ አጠቃላይ ሆስፒታል ዋና ሥራ አስኪያጅ ዶክተር ሙሉቀን ተሰፋዬ እንደገለፁት፤ የክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ከፍለው መታከም ለማይችሉ ዜጎች ተደራሽ ይደረጋል።

በዘንድሮ የክረምት የነፃ ሕክምና የበጎ አድራጎት



አገልግሎትም ከግልና መንግሥት የተወጣጡ ከ20 በላይ የሕክምና ማዕከላትን በአንድ ማዕከል በመስጠት ከ40 እስከ 50 ሺህ ሰዎች ተጠቃሚ ለማድረግ መታቀዱን አስታውቀዋል።

የኤም አር አይ፣ ሲቲስካን የሚባሉትን ውድ የሕክምና ምርመራዎችን ጨምሮ የካንሰር የማህፀን በር ቅድመ ልየታ፣ የልብ ምርመራ እና ሁሉንም የጤና ምርመራዎችን ከ150 በላይ የጤና ባለሙያዎች በማካተት በአንድ ማዕከል ይሰጣል ብለዋል።

ማንኛውም ሰው በማዕከሉ በመምጣት የጤና ምርመራ በማድረግ እራስን ማወቅ ብሎም ሕክምና ማግኘት እንደሚችሉ ገልፀዋል።

የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ ዋና ፕሮቮስት ዶክተር ሲሳይ ስርጉ በበኩላቸው፤ ለአንድ ሳምንት በሚቆየው የነፃ ሕክምና የበጎ አድራጎት አገልግሎት 30 አይነት የቅድመ ምርመራና ሕክምናዎችን ለ50 ሺህ ዜጎች የሕክምና አገልግሎት ለመስጠት መታቀዱን ጠቅሰዋል።

የትኛውም ማኅበረሰብ በተለይም ከፍለው መታከም የማይችሉ ዜጎች የራሳቸውን የጤና ሁኔታ በኮሌጁ በተዘጋጀው የምርመራ ማዕከል በመገኘት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደሚችል ገልፀዋል።

በነፃ ሕክምና አገልግሎቱ የጤና ምርምራ ሲያደርጉ ያገኘናቸው ወይዘሮ ኤልሳቤት ሰለሞን እና አቶ ጫንያለው ታለ እንደገለፁት፤ አገልግሎቱ በተለይም ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙና በቂ የሕክምና ወጪ የሌላቸው ዜጎችን ታሳቢ ያደረገ ነው።

በማዕከሉ ቀልጣፋ የሕክምና አገልግሎት እንዳገኙ ገልፀው፤ ይህ የነፃ አገልግሎት ሊበረታታ የሚገባና ተደራሽ መሆን ያለበት ተግባር መሆኑን ነው ያብራሩት ።



ፎቶ - ሀዱሽ አብርሃ

አቶ አሕመድ ሺዴ

# ጉባኤው የታዳጊ ሀገራት ድምፅ የተስተጋባበት ነው

ቃልኪዳን አሳዬ

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ የተካሄደው ዓለም አቀፉ የፋይናንስ ለልማት ጉባኤ ቅድመ ዝግጅት ጉባኤ የታዳጊ ሀገራት ድምፅ የተስተጋባበት መሆኑን የኢፌዴሪ ገንዘብ ሚኒስትር አቶ አሕመድ ሺዴ ገለጹ፡፡

የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አሕመድ ሺዴ በጉባኤው ላይ እንደገለፁት፤ በአዲስ አበባ ባለፉት አምስት ተከታታይ ቀናት ሲካሄድ በቆየው ጉባኤ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ውይይት ተደርጓል፡፡ በዚህም ለአራተኛው የዓለም አቀፉ የፋይናንስ ለልማት ጉባኤ ግብዓቶች ማሰባሰብ ተችሏል።

ታዳጊ ሀገራት ድምፃቸው ሊሰማ እንደሚገባ፣ በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ውስጥ ያላቸው ውክልና መጨመር እንዳለበትና ለልማት የሚሰጣቸው ድጋፍ ማደግ እንደሚኖርበት በጉባኤው ከተነሱ ሀሳቦች ዋናዋናዎቹ መሆናቸውን ጠቅሰዋል ፡፡

ጉባኤው የተለያዩ ሀገራት ሚኒስትሮች፣ የተመድ አባል ሀገራት ተወካዮች ተገኝተው ትልቅ ተሳትፎ ያደረጉበት ነው ያሉት ሚኒስትሩ፣ እንደ አየር ንብረት ለውጥ፣ በሀገራት መካከል ስላለው ኢኮኖሚያዊ ልዩነቶችና ሌሎችንም ዓለም አቀፍ ተግዳሮቶችን መፍትሔ አስፈላጊ እንደሆነ አፅንዖት የተሰጠበት ነው ብለዋል።

እንደ አቶ አሕመድ ገለፃ፣ የዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማትን ሪፎርም በማድረግና የፋይናንስ ትብብርን ማጠናከር ይኖርባቸዋል፡፡ በተለይም በተቋማቱ ታዳጊ ሀገራት ልዩ ትኩረትና ተሳትፎ ኖሯቸው ፍላጎታቸውን የሚመጥን ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ድጋፍ ሊደረግላቸው እንደሚገባም በጉባኤው ላይ የተነሱ ሀሳቦች ናቸው ፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ ላይ የሚደረገው የፋይናንስ ድጋፍ ውሳኔዎች በተሟላ መልኩ እየተተገበሩ አይደለም ያሉት አቶ አሕመድ፤ ሁሉን ያካተተ ዘላቂ እና የማይበገር ዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ ለማምጣት ቁርጠኝነት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡

የጉባኤው ተሳታፊዎች የአፍሪካ መዲና የሆነችው አዲስ አበባ እያስመዘገበች የምትገኘውን ልማት ተዟዙረው በመመልከት አድናቆት መቸራቸውን በመግለጽ፤ ጉባኤው ውጤታማ እንዲሆን ኢትዮጵያ ያበረከተችው አስተዋፅዖ ትልቅ እንደሆነ በተደጋጋሚ በመድረኩ መነሳቱን ገልጸዋል።

እኤአ በ2025 በስፔን በሚካሄደው ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ጉባኤ አጀንዳ የማሰባሰብ ዓላማ የነበረው ይህ ጉባኤ የአየር ንብረት ለውጥ፣ ፋይናንስ፣ የፆታ እኩልነት፣ ዘላቂና የተረጋጋ የፋይናንስ ሥርዓት፣ ፍትሐዊ የፋይናንስ ስርጭት እንዲኖር እና ሌሎች ጉዳዮችን አጀንዳ በማድረግ ተጠናቋል።

ኢትዮጵያ ጉባኤውን ለማዘጋጀት የተመረጠችው በሦስተኛው የዓለም አቀፉ የፋይናንስ ለልማት ጉባኤ በአዲስ አበባ በተካሄደበት ወቅት መሆኑ ታውቋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢትዮጵያ ሁሌም ከሶማሊያ ወንድም ሕዝብ ጎን ሆና ትቀጥላለች!

አብሮነት፣ ወንድማማችነት፣ መተባበር፣ መደጋገፍ፣ በጋራ አብሮ ከፍ የማለትና የመበልጸግ፣... የኢትዮጵያ የዘመናት የማይዋዥቅ የውጪ ዲፕሎማሲ መርህ ሆኖ የዘለቀ ነው። ይሄ አቋሟ ደግሞ ከጎረቤት ሀገራት ጀምሮ ከባለሁለት እስከ ባለ ብዙ ወገን ዲፕሎማሲያዊ ትብብርና ግንኙነት ውስጥ ሲንጸባረቅም፤ በውጤት ታጅቦም ዘልቋል፡፡

በተለይ በጋራ ተባብሮና አቅምን ደምሮ ከመሥራት እና የጋራ ሰላምን ብሎም ልማትን እውን ከማድረግ አኳያ፤ ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ጀምሮ በቀጣናው ብሎም በአህጉር እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የማይተካ ሚናዋን ተወጥታለች። እየተወጣችም ትገኛለች። ለአብነት፣ ሰላም የሁሉ ነገር መሠረት እንደመሆኑ፣ ኢትዮጵያ ከጎረቤት ጀምሮ እስከ ዓለም አቀፍ ስምሪቶች ስኬታማ ተግባር ፈጽማለች፡፡

በዚህም በኮሪያ፣ በኮንጎ፣ በሩዋንዳ፣ በሱዳን፣ በሶማሊያ እና በሌሎችም ሀገራት አህጉራዊም፣ ዓለምአቀፋዊም ተልዕኮዎችን በብቃት ተወጥታለች። በተለይ በሶማሊያ፣ በአሚሶም ጥላ ስርም ሆነ በራሷ አቅም ያበረከተችው ሚና ተኪ የሌለው ነው። በተለይ የሶማሊያ ሕዝብ ከሦስት አስርት ዓመታት በላይ ሰላምና መረጋጋት ርቆት፤ መንግሥት አልባም ሆኖ በቆየባቸው ዓመታት፤ ከዚህ ችግሩ ይወጣ ዘንድ ኢትዮጵያ ከፍ ያለ መስዋዕትነትን ከፍላለች፡፡

ኢትዮጵያ ለሶማሊያ ሕዝብ ሰላምና መረጋጋት፣ ለሶማሊያም አንድነትና ሉዓላዊነት ሳትታክት ሠርታለች። መንግሥት አልባዋን ሶማሊያ ባለ መንግሥት፣ ሰላም የራቀውንም ሶማሊያ ሕዝብ የተረጋጋ ሰላም ባለቤት እንዲሆኑ አድርጋለች። ለዚህም አንድም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአፍሪካ ሕብረት ሰላም አስከባሪ (አሚሶም) ማዕቀፍ ውስጥ ሆና፤ በሌላ በኩል በራሷ አቅም ታግዛ ወታደሮቿን በማሰማራት ለሶማሊያውያን ሰላም እና ለሶማሊያ መረጋጋት የደም እና ሕይወት መስዋዕትነት ውድ ዋጋን ከፍላለች፡፡

ዛሬም በአንድ በኩል በጎሳ ግጭት፣ በሌላ በኩል በሽብር ቡድኖች እየታመሰች ለምትገኘው ሶማሊያ፤ ኢትዮጵያ ይሄው አጋርቷን እየገለጸች ዘልቃለች። ከሶማሊያውያን ወንድም ሕዝቦች ጎን ቆማ አለኝታነቷንና አጋርነቷን እያረጋገጠች ትገኛለች። ይሄ ደግሞ አንድም ለሶማሊያ ሕዝብ ሰላምና መረጋጋት ካላት ከፍ ያለ መሻት የመነጨ ሲሆን፤ በሌላ በኩል በቀጣናው ከፍ ያለ የሰላም፣ የልማትና የትብብር ዓውድ ተፈጥሮ የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ሀብቶቻቸውን በጋራ አሰባስበው በጋር እንዲበለጽጉ እያደረገች ያለው ተግባር መገለጫ ነው፡፡

ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያ አቅምን አሰባስቦና ሀብትን አቀናጅቶ በጋራ ሠርቶ ለመበልጸግ እየሄደችበት ባለው መርህ፣ የቀጣናውን መረጋጋትና መልማት የማይሹ ኃይሎች አጥብቀው ይቃወሙታል። ከመቃወም አልፈውም ዕቅድና አካሄዷን ለማምከን የቻሉትን ሁሉ ያደርጋሉ። ለሃሳባቸው ተገዢ የሆኑ መንግሥታትንም ለዓላማቸው ማስፈጸሚያነት ይጠቀማሉ፡፡

በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ የቀጣናውን አቅም አቀናጅቶ የመልማትና የመበልጸግ መርሆዋን ለማቅናት፤ የዘላቂና ያልተቆራረጠ አስተማማኝ የባህር በር ተደራሽነቷንም እውን ለማድረግ በሕግም ሆነ በታሪካዊ ዳራም መብቶቿ ታግዛ ባቀረበችው መሠረት ከሶማሌ ላንድ ጋር የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርማለች። ይሄ መልካም እና ለቀጣናው ሰላምና ልማት ጥሩ ዕድል ሆኖ ሳለ፤ በሶማሊያ መንግሥት በኩል የተነሳው ተቃውሞ ግን በእጅጉ ከብሔራዊ ጥቅም ባፈነገጠና ለውጪ ኃይሎች በተለይም ለኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ጥቅምና ፍላጎት የተገዛ ነው፡፡

ለዚህም ነው የሶማሊያ መንግሥት የሕዝቡን ብሎም የቀጣናውን ጥቅምና ፍላጎት ከሚያስጠብቅ እሳቤ ይልቅ፣ ተግባሩን የሶማሊያን ጥቅምና ሉዓላዊነት የሚጋፋ አስመስሎ የተሰጠውን ሃሳብ ደጋግሞ ሲያነብና ሲስተጋባ የሚታየው። ይሁን እንጂ ይሄ የሶማሊያ ባለሥልጣናትን ከሀገር ይልቅ ለሌሎች ጥቅምና ፍላጎት መጠለፍ የታየበት መግለጫና ንግግር፤ በኢትዮጵያ በኩል ያለውን የጋራ ተጠቃሚነት መርህም ሆነ፣ ኢትዮጵያ ለሶማሊያ ወንድም ሕዝብ የምታደርገውን አጋርነት የሚያስቆም ያልሆነው። ከሰሞኑ ኢፌዴሪ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያወጣው መግለጫም ይሄንኑ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ባወጣው መግለጫ፤ "ኢትዮጵያ ከሶማሊያ መንግሥት መሠረተ ቢስ ውንጀላ በተቃራኒ ለሁለቱ ሀገራት ወንድማማች ሕዝቦች ሰላምና መረጋጋት ከሦስት አስርት ዓመታት በላይ ዋጋ እየከፈለች ቆይታለች። ይሄን እውነት በገፋ መልኩ የሶማሊያ ፌዴራላዊ መንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናት ግን ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ኃላፊነት የጎደላቸው መግለጫዎችን ኢትዮጵያ ላይ ማውጣታቸው ተቀባይነት የለውም። በመሆኑም፣ የሶማሊያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ባለሥልጣናት በኢትዮጵያ ላይ እየሰነዘሩት ያለውን መሠረተ ቢስ ውንጀላ እየተከታተለ ነው።

ይሁን እንጂ የሁለቱ ሀገራት ሕዝቦች ያላቸውን የደም እና የባህል ትስስር የምታስቀድመው ኢትዮጵያ፤ ለሶማሊያ መንግሥት መሠረተ ቢስ ክስ ቦታ የማትሰጥ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ የስጋት ቀጣና በሆነው የአፍሪካ ቀንድ ያለው ሕገ ወጥ የጦር መሣሪያ እና የታጣቂዎች እንቅስቃሴ በአካባቢው ሰላም ላይ ያለውን አሉታዊ ተፅዕኖ ስለምትረዳ ጉዳዩን በትዕግሥት ይዛዋለች። በትኩረትም እየተከታተለችው ነው" ብሏል፡፡

በተለይ ኢትዮጵያ ሽብርተኝነትን በመዋጋት ባላት ጽኑ አቋም በቀጣናው ግጭት የሚፈጥሩ ጉዳዮችን መከላከሏን የምትቀጥል ሲሆን፤ በዚህም ቀጣናዊ ሰላምን ብሎም ልማትን እውን ከማድረግ አኳያ ከምትሠራው ሥራ ባሻገር፣ የሶማሊያ ሕዝብ ከዚህ ሰላምም ሆነ ልማት ተጠቃሚ መሆን እንዲችል ኢትዮጵያ ወደፊትም ከሶማሊያ ወንድም ሕዝብ ጎን ሆና ትቀጥላለች!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
• ኃይሉ ሣህለድንግል
• እስማኤል አረቦ
• ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ከአመራሩ ምን ይጠበቃል?

ሰለሞን ተስፋዬ ግድየለው

አመራር ራዕይን፣ ተልዕኮንና ዕሴቶችን መሠረት በማድረግ መሪው ከሚመራቸው ሰዎች ጋር መግባባትን ከመፍጠር ይጀምራል። አንድ መሪ አንድን ተቋም ሲመራ የሚመራው ተቋም ግልጽ የሆነ ራዕይ፣ ተልዕኮና ዕሴቶች ሊኖሩት የሚገባ ሲሆን፣ ተከታዮቹም እነዚህን ራዕይ ተልዕኮና ዕሴቶችን ጠንቅቀው ማወቅ አለባቸው።

ዕውነታው ይህ ሆኖ ሳለ በበርካታ የመንግሥት መሥሪያቤቶች ራዕይ ተልዕኮና ዕሴቶች በሰሌዳ ላይ፣ በግድግዳ ላይ ወይም በቢሮ ውስጥ ተጽፈው የሚስተዋሉ ቢሆንም ቁም ነገሩ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ምን ያህል አውቀዋቸው የራሳቸው አድርገዋቸዋል የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ያስፈልጋል። በየቦታው መስቀልና መለጠፍ ሣይሆን በመጀመሪያ መሪው የተቀበላቸውና የሚያውቃቸው ሊሆኑ ይገባል። በመቀጠልም በተዋረድ ተከታዮቹ ቢቻል ባለድርሻ አካላትን ጨምሮ መቀበላቸውንና ማወቃቸውን ማረጋገጥ ይጠበቃል። የየመሥሪያቤቱ ኃላፊዎችና ሠራተኞች የመሥሪያቤቱን ራዕይ ተልዕኮና ዕሴቶች ማገናዘብና የዕለት ተዕለት ሥራቸው አካል አድርገው መንቀሳቀሳቸው ሊከሰት የሚችለውን የመልካም አስተዳደር ችግር ይቀንሳል፣ ብሎም ያስወግዳል፡፡

በመሠረቱ የአመራር ሥራ በየዕለቱና በየሰዓቱ በሚነሱት የእሣት ማጥፋት ሥራ ላይ ማሣለፍ አይደለም። የአመራር ዋነኛ ሥራ ከመሥሪያቤቱ ራዕይ ተልዕኮና ዕሴቶች ጋር የተያያዙ ቁልፍ ሥራዎች ላይ በማተኮርና በመከታተል የሚጠበቀውን ውጤት እንዲያመጡ በማድረግ የህብረተሰቡን ፍላጎት ማርካት ነው። ሁሉንም ሥራዎች ለመሥራት የሚሞክር መሪ ውጤት አያመጣም ስለሆነም የውጤትና የስኬት ሚስጥሩ ያለው በተልዕኮና በዓላማ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራትና ማሰራት መሆኑን መገንዘብ ይኖርበታል፡፡

ከአመራር ሁሉ አስቸጋሪውና ምናልባትም በሁሉም የበለጠ ትኩረት የሚያሻው የሰው ኃይል አመራር ነው። ለሠራተኞቹ /ለሰው/ ክብርና ፍቅር የማይሰጥ መሪ በሕይወቱም ሆነ በሥራው ላይ ችግር ይገጥመዋል። እንደዚህ ዓይነት መሪ ለድርጅትም ሆነ ለሀገር ውድቀት ምክንያት ነው፣ የጥሩ መሪ ዋነኛው መገለጫ የሚመራቸውን ሰዎች/ሠራተኞች/ተከታዮች/ ክብር በመስጠት ሕይወታቸውን በዕውቀትና በክህሎት ማብቃትና ለተከታዮቹ ግልጽ ሀቀኛና አርዓያ ሆኖ የመሥሪያቤቱን ዓላማ ማሣካት ነው፡፡

ጥሩ መሪዎች በመልካም ተግባራቸው በአርአያነት የሚቆሙ ባለ ራዕይና መልካም ተሞክሮ ያላቸው ንቁ ተከታዮችን የሚያፈሩና የሚያሰማሩ፣ ያላቸውን ዕውቀት ለተከታዮቻቸው የሚያስተላልፉ ሲሆን በተገላቢጦሽም በጣም ጥሩ ተማሪዎችና ሠልጣኞችም ናቸው። በመሪዎች ዘንድ ብዙ ጊዜ የሚዘነጋው በተከታዮች ዘንድ የመልካም ሥራ አፈጻጸምና ተሞክሮ ጅማሮው ቢኖርም የተገኘውን ጅማሮ ዕውቅና ሰጥቶ ምስጋና አለመስጠትና አለመሸለም ነው። ሆኖም ግን ለውጤት ዕውቅና መስጠትና ማበረታታት ሌሎች ተከታዮችም አርአያ የሆኑትን ሠራተኞች ፋና እንዲከተሉ የሚያበረታታ ከመሆኑም ባሻገር ለሠራተኞቹ/ተከታዮቹ ሞራል ቀስቃሽ በመሆኑ አስፈላጊ ነው፡፡

ጥሩ መሪ ከለውጥ ጋር አይታገልም፣ ከለውጥ አይሸሽም፣ ለውጥ ሲመጣ እጁን ዘርግቶ ይቀበላል፣ ለውጡን ለተሻለ ነገር/ሁኔታ ይጠቀምበታል። በመጨረሻም ለለውጥ እጁን ይሰጣል፣ ለለውጥ እጅን መስጠት ትክክለኛው የአመራር ዘዴ ነው፡፡

ያልተጠበቁ ክስተቶችን ማስተናገድ መቻል ለውጥን ማስተዳደር ነው። ስለሆነም መሪ ያልተጠበቁ ችግሮችን በድፍረት፣ በንቃትና በፍጥነት አጥንቶና ፈትሾ ወደ መልካም ሁኔታ መቀየር ይኖርበታል፡፡

በየቀኑ የተለመደውን ተመሣሣይ ሥራ ማከናወን አዲስ ውጤት አያመጣም፤ አዲስ ለውጥ/ውጤት ለማምጣት የሚሠራውን ሥራ መለወጥ ያስፈልጋል። ግትርነት ለለውጥ አደጋ ነው፣ ለውጥ ለማምጣትም ሆነ ለመቀበል ያስቸግራል። በአንጻሩ ተደማጭነትንና ግልፅነት ለለውጥ ያዘጋጃል፡፡

ስለዚህ ራስን ከለውጥ ጋር በማቀራረብ ለውጡን ማስተናገድ ጠቃሚ ነው። ከለውጥ ጋር ራስን ማስማማት የአንድ መሪ ትልቅ ችሎታ ነው። ለውጥን ከመቀበል ጋር ተያይዞ ውድቀት ወደ ስኬት የመሄጃ መለማመጃ መንገድ ነው፡፡

ለምሣሌ ከብስክሌት ሣይወድቅ ብስክሌት መንዳት የቻለ የለም፣ ከተወሰኑ ውድቀቶች በኋላ ግን ብስክሌትን ያለምንም ችግር መንዳት ይችላል። በተግባር ላይ ያልዋለ ዕውቀት ዋጋ የለውም፣ ስኬት የሚመጣው በምታውቀው ሣይሆን ዕውቀትን ተግባራዊ አድርገህ በምትሠራው ሥራ ነው። ለውጥ የሚፈራው ልጎዳበት እችላለሁ ከሚል ፍራቻ ሊሆን ይችላል፤ የፍርሃት መድሃኒቱ ዕውቀት ነው። ለመማር ስንፍናን ማስወገድ ያስፈልጋል ሰዎች ለማወቅ፣ ለመማር እና የመረጃ ተጠቃሚ ለመሆን ዝግጁ ከሆኑ ለውጡን ለመቀበልና ለማስተዳደር ቀላል ይሆንላቸዋል፡፡

ስለለውጥ ሲነሣ ሁልጊዜ የሚሰጠው የእንቁራሪቷ ምሣሌ ነው። «አንዲት እንቁራሪት ቀዝቃዛ ውሃ ውስጥ አድርገዋት ቀስ በቀስ ውሃውን ቢያፈሉት ከውሃው ሣትወጣ እዚያው ትሞታለች። ነገር ግን ውሃው ከፈላ በኋላ እንቁራሪቷን የፈላው ውሃ ውስጥ ቢጨምሯት አዲስ ለውጥ ስለሚሆንባት ወዲያው ዘላ ትወጣለች" ለውጥም እንዲሁ ነው። ከተውትና ከተደበቁት እያሣሣቀ ይገድላል፣ ከነቁበት ግን ሕይወት ያድናል፡፡

ለውጥ ስንል አንድ ተቋም አሁን ካለው ተቋማዊ አደረጃጀት አሠራርና አመራር ወደ አዲስ አደረጃጀት አሠራርና አመራር ለማሸጋገር የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው። የለውጥ መሪ ደግሞ ይህ እንቅስቃሴ ተግባራዊ እንዲሆን የሚታገል ነው። ለወጥ የለውጥ ካፒቴን ይሻል የሚባለው ለዚህ ነው፡፡

የለውጥ መሪ ለውጥን የህልውና ጉዳይ አድርጎ የሚወስድ ነው፣ የራሱን ማንነት በሚገባ የሚያውቅና ሌሎችን በቀላሉ የሚያነብ ጽኑ አቋም ያለው ትዕግስትን የተላበሰ፣ በራሱ የሚተማመንና ለሥራዎች ደረጃ /ስታንዳርድ/ የሚያመጣ ነው፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመቀበል በሥራ ላይ የሚያውል እና ስለ ሥራው ጠንቅቆ የሚያውቅ ነው፣ ለአዳዲስ ግኝቶች ቦታ የሚሰጥና የውጤትና ስኬት መሠረቱ የሰው ኃይል ነው ብሎ የሚያምን ነው፣ ለባልደረቦቹና ለሥራው ልዩ ፍቅር ያለውና ችግሮችን ለመፍታት የሚጥር ነው፣ ራሱን እንደ አገልጋይ የሚያይና ስህተትን እንደትምህርት ሰጪነቱ የሚወስድ ወዘተ. ነው።

ስለዚህም በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ አመራር እነዚህን መሠረታዊ መርሆች ተላብሶ በከፍተኛ ትጋት እና ቁርጠኝነት፣ ከሌብነት በፀዳ መንገድ፣ በኃላፊነት ስሜት በመንቀሳቀስ በየዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን መፍታት ይጠበቅበታል። በተለይም በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚታዩ ማነቆዎችን በመፍታት ሕዝብን ለምሬት የሚዳርጉ እንቅፋቶችን ማስወገድ ለነገ የማይባል የቤት ሥራ ነው። በዚህም አመራሩ ሕዝቡ ድረስ ወርዶ ችግር መፍታት መልመድ መቻል አለበት። ሁሉም አመራር የተሰጠው ጊዜ ሕዝብን የማገልገያ እድል መሆኑን ተረድቶ ለጠንካራ እና ፍሬያማ ለውጥ መትጋት ይኖርበታል።

ከአድሎአዊ አሠራር የፀዳች፣ ሁሉም የልፋቱን የሚቃርምባት የለውጥ ምሳሌ የሆነች ሀገር እንድትፈጠር በቀጣይ ከአመራሩ የሚጠበቀውም ይህ ነው፡፡

**ጥሩ መሪ ከለውጥ ጋር አይታገልም፣ ከለውጥ አይሸሽም፣ ለውጥ ሲመጣ እጁን ዘርግቶ ይቀበላል፣ ለውጡን ለተሻለ ነገር/ሁኔታ ይጠቀምበታል። በመጨረሻም ለለውጥ እጁን ይሰጣል፣ ለለውጥ እጅን መስጠት ትክክለኛው የአመራር ዘዴ ነው**

# ነፃ ሃሳብ

# የሠለጠነ ፖለቲካ እስከምን ድረስ?

**አዶኒስ (ከሲ.ኤም.ሲ)**

ነገን ለመለወጥ የምንችለው ሁላችንም ነገን አስበን ሥንሠራ ነው። ነገን አስበን የምንሠራው ደግሞ ትናንት ላይ ከተቸከለ አስተሳሰብ ወጥተን ነገን ማየትና ማለም፤ የጋራ ራዕይ ኖሮን ለመሻገር በጋራ መስራትና መመካከር፤ ተመካክረንም መግባባት ስንችል ነው። ይሄ ደግሞ ሕዝብ ወክዬና በሕዝብ ተመርጬ ነገ ሀገር እመራለሁ ከሚል የፖለቲካ ፓርቲና ፖለቲከኛ ጋ ሲሆን ከፍ ያለ ቦታ ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡

ምክንያቱም ፖለቲከኛ እና የፖለቲካ ፓርቲ ከግለሰባዊ እሳቤ ከፍ ያለ ነው፤ ሀገርን ማወቅ፣ ሕዝብን ማድመጥና መረዳትን፤ ሀገርና ሕዝብ የሚሹትንና ሊደርሱ የሚፈልጉትን ቀድሞ መተንበይን፤ ከትናንት ክስተትና ሁነት ላይ ዕይታን አንስቶ፣ የነገ መዳረሻን ማማተርና ለዛም ራስን ማስገዛትን፤... በብዙ መልኩ ይጠይቃል፡፡ ለዚህ ደግሞ ከእኔ እና ከፓርቲዬ ሀገሬ ትቀድማለች ብሎ መነሳት፤ ሀገር ከምንም በላይ ናት ብሎ ማሰብ ይገባል።

ይሄ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ (ዶ/ር) ንግግር፣ በአንድ ሀገር እድገትና ልዕልና፣ ለሕዝቦቿም ሁለንተናዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት እውን መሆን ዜጎች፣ በተለይም የፖለቲካ ተዋናዮች ምን ማድረግ እንዳለባቸው፤ ራሳቸውን በምን መልኩ መግለጥ እንደሚገባቸው፤ በምን አይነት እሳቤ ሀገርና ሕዝብን አስቀድመው መሄድና መሥራት እንዳለባቸው የሚያመላክትም፤ የሚያሳስብም በመሆኑ ነው ለሃሳቤ መንደርደሪያ የተጠቀምኩት፡፡

ወደራሴ ሃሳብ ስመለስ፣ መቼም በሀገራዊ ጉዳይ ላይ የሚያገባው ሰው ወይም ፓርቲ ወይም ድርጅት... ማነው የሚል ጥያቄ አላነሳም። ምክንያቱም በሀገሩ ጉዳይ የማያገባው የለምና ፤ ይህን ስል በሀገሩ ጉዳይ ላይ ተመልካች ፤ ታዛቢ፣ ምን ቸገረኝ ባይ አላዋቂ ወይም ደግሞ ሀገር ስትበጠበጥ አተርፋለሁ ባይ፣ ሁከትና የሰላም መደፍረስን የሚሻ ግን አይኖርም ብሎ አለማሰብ አይቻልም። ይኖራል ፤ ደግሞም አለ።

ግን አርቀን ማሰብ፣ ቆም ብለን በበሰለ አእምሮ አውጥተንና አውርደን መድረስና መቀበል ያለብን ነገር ቢኖር፤ ሀገር ከምንም ከማንም በላይ መሆኗን ላይ ነው። ከማንም በላይ የሆነችው ሀገራችን ሀገር ሆና እንድትቀጥል ደግሞ የእያንዳንዳችን የፖለቲካ ፓርቲ፣ አባላቶችና ደጋፊዎች ትልቅ ሃላፊነት አለብን። ይሄንን ነው ጠንቅቀን ማወቅና መረዳት ያለብን።

አንዳንዱ 'ኮ ጭር ሲል አልወድም ጥግ ይዞ በወሬ ብቻ ሲፈትል የሚውል ነው። ሌላ ሁለተኛና ሶስተኛ ሀገር ያለው ይመስል፣ ለሀገሩ እድገት ሳይሆን ውድቀት፤ ሰላምን ሳይሆን ግጭትን ሲጠምቅና የጥላቻ መርዝ ሲግት የሚያድር አይጠፋም። ግን ለምን ኩርፊያ?! ልጅ እናቱን ያኮርፋል? አኩርፎስ የት ይደርሳል። እናት እኮ ሁልጊዜም እናት ናት። እንድትጠፋ፣ እንድትጎዳ፣ እንድትጎሳቆል የሚፈልግ ማንም ልጅ አይኖርም። የእናት ጉስቁልና የሁሉም ነውና ጉስቁልናዋን ማየት የሚመኝና የሚወድ የለም። ይልቁንም የቸገራትን ሞልቶ፣ የጎበጠውን አቅንቶ አለሁ አይዞሽ ነው የምትባለው።

ሀገርም እንደዚች እናት ናት። ብዙ ጉድለት ሊኖር ይችላል (ከገዢው ፓርቲ፣ ከአስፈጻሚዎች፣ ከተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች...) ፤ ብዙ ጥፋቶች ተፈጽመው ሊሆን ይችላል፤ ወይም ደግሞ የራስን ስህተት ካለማየት የሀገር መሪን ስህተት ብቻ የመቁጠር ነገር ሊኖር ይችላል። ወይም ደግሞ እኔ ያልገባሁበት፣ እኔ ይሁን ያላልኩት ልማት ልማት አይደለም ብሎ ከማሰብ የመነጬ ሊሆን ይችላል። ምንም ይሁን ምን ግን ሁሉም ነገር ትክክል ሊሆን የሚችለው ቀና ማሰብ ስንችል፤ ቀና የሚያሰቡ ሰዎችን፣ አመራሮችንና ሌሎችንም በቀና መንፈስ መረዳትና መደገፍ ስንችል ነው።

አሁን ባለው አመራር ምንም ጥፋት ወይም ችግር የለም ብሎ ማሰብ አይቻልም። ብዙ ችግሮች አሉ። ሙስናው በየመስኩ አይን አፍጥጦ፣ ጥርሱን አግጦ ከትንሽ እስከ ትልቁ ይታያል። ይህን እውነት እየመረረንም ቢሆን መቀበል ይገባል። ነገር ግን በድፍኑ እንቃወም ካልን ቀጥ ያለው ሁሉ ጠማማ ፤ ነጩ ጥቁር ይሆንብናል። ብርሃን ከማየት ይልቅ ጨለማውን ማማተር ያመዝንብናል።

> **አ**ንዳንዱ 'ኮ ጭር ሲል አልወድም ጥግ ይዞ በወሬ ብቻ ሲፈትል የሚውል ነው። ሌላ ሁለተኛና ሶስተኛ ሀገር ያለው ይመስል፣ ለሀገሩ እድገት ሳይሆን ውድቀት፤ ሰላምን ሳይሆን ግጭትን ሲጠምቅና የጥላቻ መርዝ ሲግት የሚያድር አይጠፋም

እናም ማድረግ የምንችለው በመጀመሪያ የራስን ቀናነት ይዞ መገኘት ነው። ነገሮችን ሁሉ አጣምሞ ከመመልከት ቀና አድርጎ ማየት በእይታ ውስጥ የተጣመመ ነገር ቢኖር እንኳን እሱ የሚቃነበትን ነገር መሻት ነው። ደግሞም ያስፈልጋል። ምክንያቱም ሀገር ሀገር ናት። ለማንም የማንተዋት ምትክ የሌላት ናት። እኛም ከእሷ የማንወጣና የማንርቅ ዜጎች ስለሆንን ጉስቁልናዋን ሳይሆን እድገቷን መመኘት ለእድገቷ መሥራትና መልፋት ያስፈልጋል። የሆነ ፓርቲን፣ የሆነ መሪን ስለጠላን ብቻ ሀገራችንን የሀገራችንን ብራንድ የሆኑ ተቋማትን ስም ጥላሸት ስንቀባ መኖር አይገባም።

ምክንያቱም የትኛው ሀገር በየትኛውም መልኩ እድገታቸው አልጋ በአልጋ አልሆነም። ብዙ መስዋዕትነትን ከፍለዋል። ሁሌም የምናነሳቸው እነ ቻይና፣ ኮሪያ፣ ሲንጋፖር ድህነት በዳዴ ያስኬዳቸው ሀገሮች ነበሩ። ቻይና ዛሬ የዓለም ተጠቃሽ ሀገር የሆነችው ከዛሬ 40 እና 50 ዓመታት በፊት ምን ያህል በድህነት ውስጥ እንደነበሩ ታሪካቸውን ደረታቸውን ነፍተው፣ አንገታቸውን ቀና አድርገው ይነግሩናል። ሌላው ቀርቶ የሚልሱት የሚቀሱት አጥተው ቆዳን ምግብ አድርገው ማሳለፋቸውን እንደ ጀብዱ ያነሱታል። ዛሬ እሱ ታሪክ የለምና። ታሪክ ሰርተው ታሪካቸውን ቀይረዋልና የበለጸጉ ሀገሮች እንድንላቸው ግድ ሆኗልና።

ኢትዮጵያውያንም የጀግንነት የድል ታሪኮቻችንን፣ ካለዘመናዊ መሣሪያ ሙሉ የሀገር ፍቅርና ክብርን አንግበን በአሸናፊነት ተወጥተናል ብለን አኩሪ ታሪካችንን እንደምናወሳው ሁሉ፤ እነሱም ከድህነት ወጥተው በከፍታ ማማ ላይ የተፈናጠጡበትን ታሪክ በኩራት ያወሱታል። እውነት ነው የአንድ ታሪክ ባለቤት እንደመሆን ለትውልድ የሚያኮራ እንደ ጀግንነት የሚወሳ ነገር የለም።

ዛሬም ለሀገራችን የምንመኘው የዚህ ትውልድ የልማት አርበኛ ፤ ሀገርን ከድህነት ያወጣ ትውልድ ተብለን በታሪክ መዝገብ መስፈርን ነው። ተረጂ ሳንሆን ረጂ ሆነን በዓለም ዙሪያ የምንታወስ ሀገር መሆንን ነው። ለዚህ ደግሞ የሃሳብ አንድነት ያስፈልጋል። እኩል ስለሀገር ማሰብ የታሰበውን መልካም ነገር ወደ ተግባር መለወጥና መሥራት፣ ለልማትና ዕድገት ቅድሚያ መስጠት ፤ ወዘተ ያስፈልጋል። ለዚህ መሻታችን እውን መሆን ደግሞ ተፎካካሪና ገዢ ፓርቲ ሳንል ለአንድ ሀገር እድገት እንደ አንድ ሆነን መቆምን ይጠይቃል ።

ሆኖም አሁን አሁን አንድ የምንታዘበው ጉዳይ አለ። የተፎካካሪ ፓርቲዎች ጉዳይ። የተፎካካሪ ፓርቲዎች አለን የሚሉትና ድምጻቸውን የሚያሰሙት ምረጡን እያሉ የሚያደርቁን መቼ እንደሆነ ለማንም ግልጽ ነው። አምስት ዓመት ጠብቀው በምርጫ ወቅት ቲሸርቱ፣ በራሪ ወረቀቱ ፤ ወሬው ሁሉ ይደራል ። ሀገር በአምስት ዓመት አንድ ጊዜ ናት እስክንል ድረስ፤ የፓርቲዎች አይነትና ብዛት ሁሉ አስደማሚ ይሆናል። ይሄ ሁሉ ፖለቲካ ፓርቲ ከየት ተፈለፈለ እስክንል ።

ከምርጫው ማግስት ጀምሮ ደግሞ እስካሁን እንዳየነው ሁሉ መኖራቸው እስኪጠፋን ስማቸው ከአእምሯችን እስኪፋቅ ድረስ ድምጻቸውም ስማቸውም ይጠፋል። "አሉ እንዴ?" የሚለውን ሃሳብ እንኳን ለማንሳት የሚያስገድዱን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰበሰቧቸው ሲባሉ ብቻ ይሆናል። ካልሆነ ግን በየትኛውም ሀገራዊ ጉዳይ በየትኛውም የልማት አጀንዳ ላይ በየትኛውም መልኩ ሲሳተፉ አይታዩም።

ይሁን እንጂ በሀገራዊ የልማት ተግባር ላይ መሳተፍ (ለምሳሌ፣ በበጎ ፈቃድ ሥራ ላይ መሠማራት ማለት፣ ችግኝ ተከላ ላይ መገኘት ፤ የአረጋውያን ቤት እድሳት ላይ መሳተፍ በሌሎችም ሀገራዊ ጥሪዎች ላይ አለን ብሎ መቆም) ከተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች የሚጠበቅ ቢሆንም፤ በእኛ ሀገር ተፎካካሪ ፓርቲዎች ግን ይሄ የተለመደ ተግባር አይደለም፡፡ ይሄን ለምን ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል። ለምን አይሳተፉም ? ለምን የሀገር ጉዳይ ጉዳያቸው መሆኑን ተገንዝበው ከፊት ቀድመው ስለ ሕዝብ ጥቅም አያቀነቅኑም? ለምን መንግሥት የሚሠራውን ልማት ማበረታታት ጉዳያቸው አይሆንም? የመንግሥትን ስህተቶች ለቅሞ ማውጣት ለምን አልቻሉም... እያልን መጠየቃችን አልቀረም።

ዛሬ ሀገር እየመራ ያለው ገዢው ፓርቲ ነገ ላይኖር ይችላል። ትናንት ሀገር ሲመሩ የነበሩ መሪዎችና ፓርቲዎችም ዛሬ የሉም። ከትናንት ወዲያ ከዛም በፊት የነበሩ የሀገር መሪዎች አሁን የታሪካችን አካል ነው የሆኑት ፤ ሀገር ግን አለች። ሕዝብ ግን አለ ። ሀገር ላይ ብንሠራ ነገም ሆነ ከነገ ወዲያ ለሚመጣው ትውልድ የተመቸች ሀገር ማቆየት ይሆናል።

ዛሬ የምንጠቀመውኮ ከዚህ ቀደም የነበሩ መሪዎች የሠሩልን እና ያሠሩልን ነው፡፡ እኛም እየሠራን ያለነው የእነሱ ሥራ እርሾ ሆኖን ነው። አሁን ደግሞ ዘመኑን የዋጀ ልማት ፣ የቴክኖሎጂ እና የትምህርት እውቀት ልማት ያስፈልገናል። ለእዛ ደግሞ ተጠሪዎች እኛ ነን። ተቃዋሚና ተፎካካሪ፣ እንዲሁም ደጋፊ ሳንባባል ለሀገራችን መሥራት አለብን። ሀገራችን ላይ ሠርተን ታሪካችንን በደማቁ በማጻፍ ዐሻራችንን ማሳረፍ ይጠበቅብናል።

ይህ ሲሆን ስንኖር በስራችን ተደስተን በልማቱ ተጠቃሚ ሆነን እንቆያለን ፤ ስናልፍ ታሪክ አስቀምጠን ዐሻራችንን አኑረን ይሆናል፤ እናም የአሁን ዘመን ተፎካካሪ ፓርቲዎቻችን ሁሉንም ነገር እያዩት ያለው ከዚህ አንጻር ይሆን? ወይስ ሁሉንም ነገር በመቃወም? ሁሉንም ነገር በመቃወም ከሆነ ስህተቱ እዚህ ላይ ይሆናል። የአእምሮ ቅኝቱ መስተካከል የለበትም ?

እኔ ለሀገሬ ምን አደረኩ የሚለውን ማሰብ ያስፈልጋል። ለወቀሳና ለመቃወም ብቻ አዳራሽ ሞልቶ ትችት ማቅረብ ከጥቅሙ ይለቅ ትዝብቱ ይሰፋል። አዳራሽ ሙሉ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲ አሁንም ካሉን በምርጫ ወቅት ከ100 በላይ ተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲ ብቅ ካሉ ምነው ልማቱ ላይስ ብለን እንጠይቃለን። እንደ አንድ ዜጋ አሁን ከየት በቀሉ ማለታችን አይቀርም።

ይሄ እንዳይሆን ከፓርቲዎች ብዙ መሥራት በሀገር ጉዳይ መተባባር ይጠበቃል። ይሄ መንግሥትን መደገፍ፣ የሆነ ፖለቲካ ፓርቲን ማገዝ አይደለም ። ለሀገር መሥራት ነው። ሕዝብን ማገዝ እና መደገፍ ነው። ምነው ተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች አባላቶቻቸውን ደጋፊዎቻቸውን አስተባብረው በበጎ ፍቃድ ሥራ ላይ አይሰማሩም? ቤት ማደስ ለምን አይሳተፉም? ቤት የሚታደሰውና የሚኖርበት መቼም መንግሥት ወይም የመንግሥት ባለሥልጣን አይሆንም፤ ይልቁንም በችግር ውስጥ ያለው ምስኪን ዜጋ፣ የከተማው ነዋሪ ነው።

አርሶ አደሩን በእርሻ ሥራ፣ በእርሻ መሳሪያ ብናግዘው ያገዝነው ያንን አርሶ አደሩ የሚኖርበትን ክልል ሃላፊ ወይም የመንግሥትን አካል አይደለም፡፡ ነገ ምርቱን የሚያቀርብልንን አርሶ አደር ነው። በደም ልገሳ ብንሳተፍ የምንረዳው የመንግሥት ባለሥልጣንን አይደለም፡፡ ደም በማጣት በደም መፍሰስ ሕይወት ሰጥታ ሕይወቷን የምታጣውን እናት ነው። ሌላም ሌላም ማንሳት ይቻላል። ብዙ ብዙ መጻፍ ይቻላል።

ዋናው ነገር ግን ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሀገራዊ ጉዳይ ላይ የት ናችሁ ለማለት ነው። በሀገራዊ ጉዳይ ላይ ተቀራርቦ መነጋገር ያስፈልጋል ለማለት ነው። አሁን የመንግሥትና የተፎካካሪ ፓርቲዎች መካከል የታየው የውይይት መድረክ በውይይት መድረኩ ላይ ከመንግሥትም ሆነ ከተፎካካሪ ፓርቲዎች የተነሱ ለሀገርና ለሕዝብ ጠቃሚ የሆኑ ነጥቦች ናቸው ፡፡ እየተነጋገሩ እየተራረሙ መሄድ የሚያስችሉ ናቸው።

ይሄ ሲባል ግን በመንግሥት በኩል የመንግሥት አስተዳደር ፍጹም ትክክል ነው ገፌ ምክንያቶች የሉም ለማለት አይቻልም። ይኖራሉ፤ መቼም ፉክክር ብሎ ሁሉንም ነገር አልጋ በአልጋ አድርጉ መጠበቅ አይቻልም። ችግሮች ያጋጥማሉ፣ ጎርባጭ መሰናክሎች ይኖራሉ፤ እነሱን በጥበብና በዘዴ እያለፉና እየተነጋገሩ ማስቀረት ባይቻል እንኳን መቀነስ ይቻላል። ምክንያቱም አርቀን የምናማትረው ሀገር አለችንና ነው።

በሀገራችን ባልተለመደ መልኩ በመንግሥት ከፍተኛ የሥራ ሃላፊነት ቦታዎች የተፎካካሪ ፓርቲዎች ተወካዮች ተቀምጠዋል። መቀመጣቸው ጠቀመ እንጂ ሀገርን አልጎዳም። ይልቁንም የፖለቲካ ምህዳሩን የሚያሰፋ ጅምር ጭላንጭል፤ የሠለጠነ የፖለቲካ ምህዳርና አሠራርን የሚፈጥር ነው። ይሄ እንዲሰፋ ለማድረግ ጥሩ ተፎካካሪ ሆኖ መቅረብ ያስፈልጋል። ጥሩ ተፎካካሪ መሆን መቃወም ብቻ አይደለም።

የሠለጠነ ፖለቲካ ማለትም ይሄው ነው፤ ምክንያቱም የሠለጠነ ፖለቲካን የሚያራምድ ግለሰብና ቡድን የተሻለ ሃሳቦችን የሚያመነጭ፣ ችግሮቹን ፈልፍሎ በማውጣት እንዲታረሙ የሚያደርግ፤ ጠንካራ የፖሊሲ ሃሳብ አመንጪ ነው። በመነጋገር እና በመወያየት ለውጥ ለማምጣት የሚሞክር ነው። በመሆኑም ይሄን እውን የሚያደርግ በሁሉም መልኩ የሠለጠነ ፖለቲካ ከሁሉም በፊት ሀገርን የሚያስቀድም መሆን አለበት። ሰላም!

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# በባህላዊ ህክምና ለብዙዎች መፍትሄ የሆኑት ሎሬት

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ኢትዮጵያ ከምትታወቅባቸው ሀገር በቀል ዕውቀቶች መካከል የባህል ህክምና፣ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ፣ ቁጠባ፣ ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓት፣ ዘመን አቆጣጠር፣ ዕደጥበብና የእርቅ ሥርዓት ተጠቃሽ ናቸው። የዕለቱ ትኩረታችንም ለሀገር ግንባታ ጉልህ ሚና ካላቸው ሀገር በቀል ዕውቀቶች መካከል አንዱ በሆነው በባህል ህክምና ላይ ልናደርግ ወደናል፡፡

በሀገሪቱ በርካታ ቁጥር ያላቸው ባህላዊ ሀኪሞች ስለመኖራቸው ይታመናል። ከእነዚህም መካከል አለሙ ተጨማሪ ምግብ ማቀነባበሪያ መሸጥ የግል ኢንተርፕራይዝ አንዱ ነው። ድርጅቱ ከተለያዩና ሀገር በቀል ከሆኑ የምግብ ቅመማቅመሞች የተቀነባበሩ መድሃኒቶችን ያመርታል። የምግብ ውጤቶችን መሠረት ያደረገው ይህ የባህል ህክምና ከብዙ ጥናትና ምርምር በኋላ ለበርካታ ህመሞች መድሃኒት መሆን ችሏል። በመከላከል ረገድም እንዲሁ ውጤት እያስመዘገበ ይገኛል።

ብርቱ በሆነ ምርምርና ጥናት እንዲሁም ጥረት የባህል ሀኪም የሆኑት የዕለቱ እንግዳችን በፈጠራ ሥራቸው የሎሬትነት ማዕረግ አግኝተዋል። ለማወቅ፣ ለመመራመርና መፍትሔ ለመሆን ያላቸው ውስጣዊ ተነሳሽነት ዛሬም ትኩስ ነው። የመድሃኒቱን ውጤት ለማግኘት 13 ዓመታትን የፈጀ ጥናትና ምርምር አድርገዋል። ፈቃድ አግኝተው ወደ ሥራ ለመግባትም እንዲሁ ሰባት ዓመታት ታግሰው ደጅ ጠንተዋል። በድምሩ ከሁለት አስርት ዓመታት ትግል በኋላ ዛሬ ውጤት ያገኙበትን የባህል መድሃኒት ለማህበረሰቡ ተደራሽ ማድረግ ችለዋል፡፡

ገና በልጅነት በውስጣቸው ይንቀለቀል የነበረውን ፍላጎት በትምህርት አጎልምሰው ዛሬ የባህል ሀኪም መሆን የቻሉት እንግዳችን፤ ከልጅነታቸው ጀምረው ለህክምና ዕውቀት ልባቸው ክፍት ነበር። ከልባቸው መከፈት ባለፈም በቤተሰብ እቅፍ ውስጥ እያሉ ጀምሮ ጥሩ አጋጣሚዎች ነበሯቸው። ከቤተሰብ በተጨማሪም መምህር ሆነው ሲያገለግሉ ስለ ባህል ህክምና በሚገባቸው ልክ ለማወቅ፣ ለመረዳትና ለመመራመር ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል። አብዛኛውን ጊዜያቸውን ለንባብና ለምርምር በማዋል ከጎሬ እስከ ሰንዳፍ የባህል ህክምናን ዕውን ለማድረግ ሲታትሩ የኖሩት የዕለቱ እንግዳችን ሎሬት አለሙ መኮንን ይባላሉ። ከጎሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተጀመረው የሎሬት አለሙ ትጋት መዳረሻውን ሰንዳፋ በማድረግ ፍሬ ማፍራት ጀምሯል።

### ትውልድና ዕድገት

ሎሬት አለሙ መኮንን ተወልደው ያደጉት ጥንታዊና ታሪካዊ በሆነችው ጎሬ ከተማ ነው። የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውንም ተወልደው ባደጉበት ጎሬ ከተማ ላይ ተከታትለዋል። በጅማ መምህራን ትምህርት ኢንስቲትዩትም እንዲሁ የመምህርነት ሥልጠና ወስደው የመምህርነት ሙያን አግኝተዋል። ትምህርት ሚኒስቴር የሰጠውን ዕድል ተጠቅመው ላቦራቶሪ ቴክኒሻንነትንም አክለውበታል። በመምህርነት ዘመናቸው የኬሚስትሪ መምህር እና የላቦራቶሪ ባለሙያ በመሆን ላለፉት 28 ዓመታት ያገለገሉት ሎሬት አለሙ፤ የማስተማር ሥራን ‹‹ሀ›› ብለው የጀመሩት ጋምቤላ ቢሆንም በተማሩበት ትምህርት ጎሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትም የማስተማር ዕድል ገጥሟቸው አስተምረዋል።

ጎሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የነበራቸውን ቆይታ በሙሉ ከመደበኛው የማስተማር ሥራቸው ጎን ለጎን ስለ ባህላዊ ህክምናና መድሃኒቶች ሲያጠኑ ኖረዋል። ስለባህላዊ ህክምና ያለመታከት ሲመራመሩ የቆዩት ሎሬት አለሙ በወቅቱ በርከት ያሉ መነሻ የሚሆኑ ፎርሙላዎችን አሰባስበዋል። ከጎሬ ወደ ሰንዳፋ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዝውውር በሄዱበት ጊዜ ያሰባሰቧቸውን ፎርሙላች ይዘው በመጓዝ ከማስተማር ሥራቸው ጎን ለጎን ምርምርና ጥናታቸውን በማስቀጠል ዛሬ ላይ ደርሰዋል።

### መሠረት የጣለው የአባት ምክር

ከተማረና የህክምና ባለሙያ ከሆነ ቤተሰብ የተገኙት ሎሬት አለሙ፤ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ተምሮ የመለወጥ ውጥን ይዘው ነው ያደጉት። በተለይም ውስጣቸው የነበረውን ፍላጎት ማውጣት እንዲችሉ ወላጅ አባታቸው ትልቁን ሚና ተጫውተዋል። ወላጅ አባታቸውም የተለየ ቀረቤታ የነበራቸው በመሆኑ እንደጓደኛሞች ነበሩ። ከትምህርታቸው ጎን ለጎን የወላጅ አባታቸውን ሥራ በቅርበት የመከታተል፣ የመጠየቅና የመረዳት አጋጣሚው የተፈጠረላቸው ሎሬት አለሙ፤ ወላጅ አባታቸው መድሃኒት ቤት መክፈት በመቻላቸው ነበር። ለዚህም ነው ብዙ ጊዜያቸውን በመጠየቅ የሚያሳልፉት፡፡



በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግሥት በሀገሪቱ የጤና ተቀሚት ተደራሽ ባለመሆኑ የጤና ተቋማት፣ ክሊኒኮች በተለይም ፋርማሲዎች ተስፋፍተው እንደነበር ያስታወሱት ሎሬት አለሙ፤ በወቅቱ በመላው ሀገሪቷ የጤና ተቋማትን ለማዳረስ በሚል መንግሥት ፋርማሲ መክፈት ለሚፈልጉ ሀኪሞች ፈቃድ መስጠቱን አጫውተውናል። በወቅቱ የጤና ባለሙያ የነበሩት ወላጅ አባታቸው ዕድሉን ተጠቅመው ፋርማሲ መክፈት በመቻላቸው ህክምናን በቅርበት መረዳት አስችሏቸዋል። ወቅቱ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በመላው ኢትዮጵያ ፋርማሲዎችና ክሊኒኮች የተስፋፉበት ነበር።

ገና ከልጅነታቸው ጀምሮ መድሃኒቶችን በቅርብ እየተመለከቱ የማደግ አጋጣሚ የተፈጠረላቸው ሎሬት አለሙ፤ መድሃኒት ነክ ነገር ይስባቸው ጀመር። ስለመድሃኒት ከመረዳት ባለፈ ቀስ በቀስ ፍላጎት እያደረባቸው ሲመጣ ታውቋቸዋል። በመድሃኒት ቤት ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን በሙሉ ጠንቅቀው የሚያውቁት ሎሬት አለሙ፤ መድሃኒት የመሥራት ፍላጎት እንዲኖራቸው ያደረገ አንድ አጋጣሚ የተፈጠረው በወላጅ አባታች መድሃኒት ቤት ውስጥ ነበር።

አጋጣሚውን መነሻ በማድረግ ታዲያ መድሃኒት የመሥራትና ህክምና ውስጥ መግባት ፍላጎት እንዳላቸው ለወላጅ አባታቸው አጫወቷቸው። ወላጅ አባታቸውም መድሃኒት የመሥራት ፍላጎት ካላቸው በዋናነት እጽዋትና ምግብ ላይ ትኩረት አድርገው ማጥናት እንደሚገባቸው አባታዊ ምክራቸውን ከሙያ ጋር በማስተሳሰር አስረድተዋቸዋል።

### ከትምህርት የተገኘው ውጤት

‹‹የተማሩ ሰዎች የባህሪና የሥራ ለውጥ ማምጣት አለባቸው›› የሚሉት ሎሬት አለሙ፤ ትምህርት ሁለት መሠረታዊ ለውጦችን የሚያመጣ ስለመሆኑ በጽኑ ያምናሉ። አንደኛው የሰውዬውን ባህሪ የሚቀይር ሲሆን፤ ሁለተኛው የሥራ ለውጥ የሚያመጣ ነው። ይህ ካልሆነ ግን ሰውዬው ተማረ ማለት አይቻልም። ምክንያቱም በልጅነቱ ያለው ባህሪ እና ከተማረ በኋላ የሚኖረው ባህሪ የተለያዩ ናቸው። ለዚህም ነው በመማሬ ምክንያት በሕይወቴ የባህሪና የሥራ ለውጥ ማምጣት ችያለሁ ይላሉ።

ትምህርት በተለይም የባህሪ ለውጥ ለማምጣት በብዙ የሚያግዝ በመሆኑ ውስጣቸው ያለውን ዕውቀት አውጥተው መጠቀም እንዲችሉ በር ከፍቶላቸዋል። በተለይም ይላሉ ‹‹በተለይም ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ ያስተማሩኝ መምህራኖቼ ውስጤ ያለውን ዕውቀት እንዳወጣ አግዘውኛል። መምህር ተማሪዎች ውስጣቸው ያለውን ዕውቀት ማውጣት እንዲችሉ መንገድ የሚያሳይ ነው። ስለዚህ ውስጤ ያለውን ዕውቀት አውጥቼ መጠቀም እንድችል መምህራኖቼ በብዙ አግዘውኛል›› ያሉት ሎሬት አለሙ በትምህርት ቤት ከመምህራኖቻቸው ካገኙት ዕውቀት በተጨማሪ ከወላጅ አባታቸው ያኙት ምክር ዛሬ ለደረሱበት ደረጃ ጉልህ አበርክቶ እንዳለው ያምናሉ፡፡

### መነሻ ሃሳብ

ገና ተማሪ እያሉ ለዘመናዊ ህክምና ቅርብ ሆነው ያደጉት ሎሬት አለሙ፤ ሰዎች ከሚገጥማቸው ህመም ለመፈወስ ወላጅ አባታቸው ጋር በመምጣት የተለያዩ መድሃኒቶችን ገዝተው ሲጠቀሙ አስተውለዋል። ከትምህርት የሚተርፍ ሙሉ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ከወላጅ አባታቸው ጋር በመሆኑ መድሃኒት ቤት ውስጥ ብዙ ነገር አስተውለዋል። በዚህ ጊዜ መድሃኒት ማለት በአብዛኛው ፈዋሽ እንደሆነ ተረድተዋል። ይሁንና አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ያለማቋረጥ መድሃኒት ሲወስዱ ተመልክተዋል። ይህን ያስተዋሉት ሎሬት አለሙ፤ በወቅቱ ለምን የሚል ጥያቄ አቅርበዋል።

ወደ መድሃኒት ቤት ከሚመጡ ደንበኞች መካከል አንደኛው የስኳር ታማሚ በመሆኑ ዕለት ዕለት ወደ መድሃኒት ቤት በመምጣት መርፌ ይወጋሉ። ይሄን ጊዜ ‹‹እገሌ ለምን አይድኑም›› የሚል ጥያቄ ያቀረቡት ሎሬት አለሙ፤ ወደ ፋርማሲው ከሚመጡ በርካታ ደንበኞች መካከል ቀልባቸውን የሳቡት እኚህ የስኳር ታማሚ ነበሩ። ሰውዬው የወላጅ አባታቸው ጓደኛ በመሆናቸው ጭምር ልባቸው

> **ወደ መድሃኒት ቤት ከሚመጡ ደንበኞች መካከል አንደኛው የስኳር ታማሚ በመሆኑ ዕለት ተዕለት ወደ መድሃኒት ቤት በመምጣት መርፌ ይወጋሉ**

ክፉኛ ተነክቷል። አባትም የስኳር ታማሚ እንደሆኑና በወቅቱ የነበረው የስኳር ህክምና ደግሞ የዕድሜ ልክ ህክምና እንደሆነ አስረድተዋቸዋል። ይህን የተረዱት ሎሬት አለሙ፤ የበለጠ በማዘን ለምን? እንዴት? የሚሉ ጥያቄዎች ከአዕምሯቸው ጓዳ ሲርመሰመስ ተሰምቷቸዋል።

ስኳር ታማሚዎች መድሃኒቱን በሕይወት ዘመናቸው እስካሉ ድረስ የሚጠቀሙት እንደሆነና መድሃኒቱን ካቋረጡ ግን በሽታው የሚገድላቸው እንደሆነ ከወላጅ አባታቸው የተረዱት ሎሬት አለሙ፤ በልጅነት ትንሹ ልባቸው ክፉኛ በማዘን ግን ደግሞ መፍትሔ ለመፈለግ ወሰኑ። ኀዘናቸውን ያስተዋሉት ወላጅ አባታቸውም ሳይንስ እያደገ እንደሚሄድና ወደፊት የሚሻሻል መሆኑን፤ ዛሬ ያልተገኘው መድሃኒት ነገ እንደሚገኝ ሳይንስ፣ ምርምርና ጥናት አንድ ቦታ እንደማይቆም ሊያስረዷቸው ሞከሩ። ይህን ጊዜ አንዳች ተስፋ በውስጣቸው ሲያቆጠቁጥ ተሰማቸው። እናም ወደፊት የህክምና ሥራ በመስራት ለችግሮች መፍትሔ ለመሆን ለራሳቸው ቃል ገቡ። ቃላቸውን በተግባር ለማዋልም የወላጅ አባታቸውን ምክር በልባቸው ሰንቀው እጽዋትና ምግብ ላይ ትኩረት ለማድረግ ወስነዋል፡፡

### መምህርነትና ምርምር

የወላጅ አባታቸውን ምክር በልባቸው ያኖሩት ሎሬት አለሙ፤ በትምህርት ጊዜያቸውም ሆነ በሥራ ሕይወታቸው ሁሉ ምክሩን ተግባራዊ ማድረግ የሚችሉባቸውን አጋጣሚዎች አሟጠው ተጠቅመዋል። በተለይም የመምህርነት ሙያቸው ለጥናትና ምርምር ትልቅ ድጋፍ የነበረው በመሆኑ ብዙ ጥረት አድርገዋል። ሌት ተቀን በማንበብ፣ በመመራመር፣ በማጥናትና በመሞከር ውጤት እስኪያገኙ ድረስ ብዙ ለፍተው ወጥተውና ወርደው ውጤት አግኝተዋል።

ልባቸው የተነካበት የህክምና ሙያን ከወላጅ አባታቸው ባገኙት ምክር ተግባራዊ ማድረግ የጀመሩት መምህር እያሉ ነበር። ጎሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህር የነበሩት ሎሬት አለሙ ከመደበኛው የመምህርነት ሥራቸው ጎን ለጎን ቤተመጽሃፍት እና ቤተሙከራ በመግባት ስለ ዕጽዋትና ስለ ምግብ የሚያስረዱ መጽሃፎችን ለይተው ማንበብና መመራመር ጀመሩ። በመጀመሪያው ንባብ ያገኙትና የሳባቸው ቅመማቅመም ነበር። የቅመማቅመም አይነቶችን እና ያላቸውን ጠቀሜታ በዝርዝር ማንበብ ቀጠሉ። ቅመማቅመም በብራዚል፣ በህንድ፣ በአሜሪካና በጀርመን እንዲሁም በሌሎች ሀገራት የተጠኑ በርካታ ጥናቶችን አግኝተው አንብበዋል። በተለይም በህንድና በብራዚል የተጠኑት ጥናቶች በርከት ያሉ ጉዳዮች ያነሱና ሳቢ እንደነበሩ ያስታውሳሉ፡፡

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# በባህላዊ ህክምና ለብዙዎች መፍትሄ...

ከገጽ 6 የዞረ

እነዚህን ጥናቶች በሚያነቡበት ጊዜ ታዲያ የባህል ህክምናው የበለጠ የሳባቸው ሎሬት አለሙ፤ ለምግብ ማጣፈጫነት በቤት ውስጥ የምንጠቀማቸው ቅመማቅመሞች በርካታ ጥቅሞች እንዳላቸውና መድሃኒት መሆን እንደሚችሉ ተረድተዋል። ለዚህም ነው ጉዳዩን ጠበቅ አድርገው በመያዝ ሥራቸውን ቀጥለዋል። በወቅቱም ለቁጥር የበዙ ፎርሙላዎችን በማዘጋጀት ስለቅመማቅመሞች ጥቅም በብዙ ተረድተዋል፡፡

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ወደ ሰንዳፋ ሁለተኛ ደረጃ ተዘዋውረው የመጡት ሎሬት አለሙ፤ ሰንዳፋ ተመድበው ሲያስተምሩና ቅመማቅመሞች ላይ የጀመሩትን ምርምር ሲያደርጉ ቆይተዋል። ሰንዳፋ ላይ እንደ ጎሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ባይሆንም የተወሰኑ መጽሐፍቶችን አግኝተው ማንበብና መመራመራቸውን ቀጠሉ። የሰንዳፋ ቤተመጽሐፍት ብዙ አላስደሰታቸውም፤ ያም ቢሆን ታዲያ በውስጣቸው የሚንቀለቀለውን ሃሳብ ዳር ለማድረስ በየጊዜው አዲስ አበባ በመምጣት በየቤተመጽሐፍቱ ተዘዋውረው ማንበብና ስለ ቅመማቅመም ማጥናታቸውን መደበኛ ሥራቸው እስኪመስል ብዙ ጊዜ ሰጥተው ተከታትለዋል።

በተለይም ጥረታቸው ፍሬ እንዲያፈራ በብዙ የታተሩት ሎሬት አለሙ፤ የህንድ መጽሐፍትን በስፋት አገላብጠዋል። ለዚህም ምክንያታቸው ህንዶች በቅመማቅመም የታወቁ በመሆናቸው ነው። የተለያዩ መጽሐፍቶችን ከህንድ ኤምባሲ ማግኘት የቻሉት ሎሬት አለሙ፤ ጎሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሆነው የጀመሩትን ፎርሙላ ሰንዳፋ ላይ ንባብ ጨምረው ማስቀጠልና የበለጠ ማዳበር ችለዋል። ገና በልጅነት በውስጣቸው የተጠነሰሰውን የህክምና ፍላጎትም ከዘመናዊ ህክምናው በበለጠ ወደ ባህላዊ ህክምና እንዲያዘነብሉ ሁኔታዎች ፈቅደውላቸዋል።

**የመድሃኒት ግኝት**

መምህር ከመሆናቸው ባለፈ የባህል ሀኪም የመሆን ህልማቸውን ዕውን ለማድረግ በብዙ ሲያነቡ ሲመራመሩና የተለያዩ ፎርሙላዎችን ሲያዘጋጁ የኖሩት ሎሬት አለሙ፤ ትልቁ ትኩረታቸው ገና በልጅነት ውስጣቸውን ለነካው የስኳር ህመም መፍትሔ ማፈላለግ ነበር። ባደረጉት ምርምርና ንባብም ለስኳር ህመም ውጤት ማግኘታቸውን ይናገራሉ። ሰዎች በቤት ውስጥ ለምግብ ማጣፈጫነት የሚጠቀሟቸውን ቅመማቅመሞችን በመቀላቀል ከተለያዩ ህመሞች ለመፈወስ እንዲሁም ለመከላከል ትልቅ አቅም እንዳላቸው ባደረጉት ምርምር ተረድተዋል። በተለይም ለስኳር ህመምና ከሰውነት ውስጥ ዩሪክ አሲድን ለማጥፋት ባደረጉት ከፍተኛ ጥረት ውጤት ማግኘት እንደቻሉ ይናገራሉ፡፡

በአሁኑ ወቅትም ከቅመማቅመም ብቻ የተዘጋጁ ተጨማሪ ምግቦች በሚል ስያሜ ያዘጋጁት ምግብ ለተለያዩ ህመሞች መፍትሔ እየሆነ መምጣቱን ተጠቃሚዎች ምስክር ናቸው። እነዚህ መድሃኒትነት ያላቸው ተጨማሪ ምግቦች አሁን ላይ ማህበረሰቡ እየለመዳቸው መሆኑን ያነሱት ሎሬት አለሙ፤ በተለይም ከስኳር ጋር ተያይዘው ለሚመጡ ህመሞች መፍትሄ ስለመሆኑ ተናግረዋል። ተጨማሪ ምግብ የሚል ስያሜ የተሰጣቸው መድሃኒቶችም ምንም አይነት የጎንዮሽ ጉዳት የማያስከትሉ ስለመሆናቸው ከምግብና መድሃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን ማረጋገጫ እንዲሁም ከአዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ፓተንት አግኝተዋል።

ከተለያዩ ቅመማቅመሞች የተዘጋጁት መድሃኒትነት ያላቸው እነዚህ ምግቦች በተለይም ለስኳር ህመም መፍትሔ እየሆኑ ነው። ይህም ማለት ስኳሩን ሙሉ ለሙሉ ማጥፋት ባይቻልም የስኳር ተጓዳኝ ህመሞችን ለማስወገድና የስኳሩ መጠን እንዲስተካከል ያደርጋል። በቤት ውስጥ ለምግብነት ከሚያገለግሉ ቅመማቅመሞች መካከል ፌጦ፣ ቅሩንፉድ፣ ጥቁር አዝሙድ፣ አብሽና ቀረፋ ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ቅመሞቹ አንድ ላይ ተዋህደው በምግብ መልክ የተዘጋጁና ህመም የሚያስወግዱ ውህዶች ናቸው። እነዚህ ውህዶችን ወደ ገበያ ለማውጣት ፈቃድ ያገኙት ተጨማሪ ምግብ በሚል ሲሆን በአሁኑ ወቅትም

> **ሚልፋን ሁለት፤ ስብን ለማስወገድና ክብደትን ለመቀነስ እንዲሁም ለኮሎስትሮልና ለደም ግፊት ጠቃሚ ሲሆን፤ ጨይጂን የሚል መጠሪያ ያለው ለሪህ /ዩሪክ አሲድ/ ለአርትራይተስ፣ ለጉልበትና እግር እብጠት፣ እግር እጅና ሰውነት ውስጥ ለሚያቃጥል፣ ለወገብ ህመምና ለሌሎችም በመድሃኒትነት የሚያገለግል ተጨማሪ ምግብ ነው**

ተጨማሪ ምግብ በሚል ማህበረሰቡ አውቋቸው እየተጠቀመባቸው ነው። ይህ መድሃኒትነትን በውስጡ የያዘው ተጨማሪ ምግብ ሚልፋን አንድ፣ ሚልፋን ሁለትና ጨይጅን በመባል በሶስት ይከፈላል። ሶስቱም የተለያየ አገልግሎት ሲኖራቸው ሚልፋን አንድ፤ ለስኳር ተጓዳኝ ህመሞች፣ ለኩላሊትና ለጉበት ችግሮች፣ ለአንጀት ውስጥ ትላትሎች፣ ለነርቭ ችግር፣ የካንሰር ሴሎችን መራባት ለመቀነስ፣ የሽንት ፊኛ ችግር፣ ለኪንታሮት፣ ለሳይነስና አስም፣ ለማድያትና ለጨጓራ ባክቴሪያ መድሃኒትነት የሚያገለግል ነው።

ሚልፋን ሁለት፤ ስብን ለማስወገድና ክብደትን ለመቀነስ እንዲሁም ለኮሎስትሮልና ለደም ግፊት ጠቃሚ ሲሆን፤ ጨይጂን የሚል መጠሪያ ያለው ለሪህ /ዩሪክ አሲድ/ ለአርትራይተስ፣ ለጉልበትና እግር እብጠት፣ እግር እጅና ሰውነት ውስጥ ለሚያቃጥል፣ ለወገብ ህመምና ለሌሎችም በመድሃኒትነት የሚያገለግል ተጨማሪ ምግብ ነው።

ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ማህበረሰቡ ይዘው የቀረቡት የምርምር ውጤት ከላይ ተዘረዘሩትን ህመሞች ማስወደግ ችሏል። ነገር ግን መድሃኒቶቹ ሲወሰዱ ኪሎ በጣም ያወርድ ነበርና ይህን ለማስተካከል ተጨማሪ ጥናት አድርገዋል። መድሃኒቱን የተጠቀሙ ሰዎች ከህመማቸው መፈወስ ቢችሉም ክብደታቸው በጣም ቀንሷል። በዚህ ምክንያት ተጨማሪ ምርምር ያስፈለጋቸው ሎሬት አለሙ፤ ተጨማሪ ምርምርና ጥናት በማድረግ ከመድሃኒት ውስጥ ክብደትን ሊያወርዱ የሚችሉ ቅመሞችን በመለየት ከውስጥ አውጥተዋል። በመሆኑም መድሃኒቱ ክብደትን ሳይቀንስ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት አስችሏል። ወደ ማህበረሰቡ ከማምጣቸው አስቀድመው መድሃኒቱን በራሳቸውና በዙሪያቸው ባሉ ወዳጆቻቸው የሞከሩት ሎሬት አለሙ፤ ያደረጉት ሙከራ ሁሉ ውጤታማ ሲሆን አስተውለዋል። በዚህም የበለጠ በመበረታታት ብዙ ጥናትና ምርምር በማድረግ ቅመማቅመሞችን አዋህደው ለመድሃኒትነት አውለዋል፡፡

ለስኳር ህመም ትልቅ ትኩረት ሰጥተው የሚያጠኑት ሎሬት አለሙ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ የሞከሩት ባህላዊ መድሃኒት ለስኳር ህመም ነበር። ስኳር ታማሚ ለነበረ አንድ ሰው የሰጡት መድሃኒት ስኳሩን ሙሉ ለሙሉ ማስወገድ ባይችልም ከስኳር ጋር ተያያዥ የሆኑ ህመሞችን ሊያጠፋለት ችሏል። ከፍ ዝቅ እያለ የነበረው የስኳሩ መጠንም እንዲሁ መረጋጋትና መስተካከል ችሏል። ይሄኔ ሞራል ያገኙት ሎሬት አለሙ፤ በርትተው በመሥራት የቀጠሉት ከዛን ጊዜ ጀምሮ ነው። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት ተለያዩ ቅመሞችን በማቀላቀል ለተለያዩ ህመሞች መድሃኒት መሥራቱን አጠናክረው ቀጥለዋል፡፡

ለመድሃኒትነት ብለው የሚቀላቅሉት ቅመማቅመሞችም በዓለም ደረጃ የሚታወቁና የተመዘገቡ በመሆናቸው ጉዳት የላቸውም። ‹‹ቅመሞቹ ሲቀላቀሉ የማዳን አቅማቸው ከፍ ይላል›› የሚሉት ሎሬት አለሙ ባህላዊ ህክምናውን ከዘመናዊ ህክምና ጋር በማስተሳሰር ይሠራሉ። ይህም ማለት ደንበኞቻቸው ከሚጠቀሙት ባህላዊ መድሃኒት በተጨማሪ ዘመናዊ ህክምናው ተከታትለው በየሶስት ወሩ ውጤት እንዲያመጡ ያደርጋሉ። በተለይም የስኳር ታማሚዎች ከባህላዊ መድሃኒቱ ጎን ለጎን በዘመናዊ ህክምና ስኳሩ ያለበትን ደረጃ በየጊዜው እንዲያቀርቡ ይደረጋል። በዚህም አበረታች ውጤት አግኝተዋል። ደንበኞችም ጤናቸው እየተሻሻለ ስለመሆኑ ይናገራሉ።

**የባህል ህክምናን ለማዘመን**

የማህበረሰብን ጤና ለመጠበቅ ባህላዊ ህክምና ጉልህ ድርሻ አለው የሚሉት ሎሬት አለሙ፤ ባህላዊ ዕውቀቶች ከዘመናዊ ዕውቀት ጋር ተሳስረው መሄድ እንዳለባቸውና ሊሰራባቸው የግድ እንደሆነ በጽኑ ያምናሉ። ሀገር በቀል ዕውቀት የሀገራዊ ችግር መፍቻ ቁልፍ መሆኑን በማመን የፈጠራ ሥራዎች መበረታታት እንዳለባቸው ሲያስረዱ፤ መንግሥት አሁን ላይ ለፈጠራ ሥራ የሰጠው ትኩረት የሚበረታታ መሆኑን በመግለጽ ነው።

የፈጠራ ሥራቸውን ለመሥራት የሚያስችላቸውን 70 ካሬ ሜትር ስፋ ያለውን ቦታ ከመንግሥት እንዳገኙ የገለጹት ሎሬት አለሙ፤ በአሁኑ ወቅት መድሃኒትነት ያለውን ተጨማሪ ምግብ በማምረት ማህበረሰቡጋ እየደረሱ ነው። ይሁንና አሁን ላይ የተጠቃሚዎች ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ ምክንያት ሥራውን የማስፋት ዕቅድ አላቸው። በመሆኑም ባህላዊ ህክምናውን ማስፋት የግድ እየሆነ መጥቷል። በተለይም የመድሃኒቶቹን አመራረት ዘመናዊ ለማድረግ የቦታ ጥያቄ አቅርበዋል። ወደፊት የቦታ ጥያቄያቸው ከተመለሰ መድሃኒትነት ያላቸውን ቅመማቅመሞች መፍጫና ትልቅ አቅም ያለው መቀላቀያ ዘመናዊ ማሽን በመትከል በስፋት የማምረትና ህክምናውን የማዘመን ዕቅድ አላቸው፡፡

ባህላዊ ህክምናውን በማዘመን በቀጣይ ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ ለመሸጋገር ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ያሉት ሎሬት አለሙ፤ የምርምር ሥራቸውን ‹‹ሀ›› ብለው የጀመሩት ከእጅ ወደ አፍ በሆነ የመምህር ደመወዝ እንደነበር አስታውሰው፤ ከመነሻ ካፒታል የበለጠ ለሀገር በቀል ዕውቀትና ለባህላዊ ህክምና ከፍተኛ ተነሳሽነትና ውስጣዊ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን ተናግረዋል። ይሁንና በአሁኑ ወቅት ህክምናውን ለማዘመን ካላቸው ዕውቀት፣ ልምድና ተነሳሽነት በተጨማሪ መነሻ ካፒታል ጭምር ያላቸው በመሆኑ ባህላዊ ህክምናውን በማዘመን ጤናማ ማህበረሰብ ለመፍጠር በሚደርጉት ትግል የሚመለከተው አካል አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግላቸው ጠይቀዋል።

**ውጤት**

በስኳር ህመምና በዩሪክ አሲድ ውጤታማ መሆን እንደቻሉ የሚናገሩት ሎሬት አለሙ፤ መድሃኒቱን በትክክል የሚጠቀሙ ሰዎች ውጤት አግኝተዋል። በየሶስት ወሩ ክትትል አድርገው የሚያመጡት ውጤትም ጤናቸው እየተሻሻለ መሆኑን ያሳያል። አብዛኛው ሰው በተለይም ዩሪክ አሲድ ከውስጡ መጥፋት ችሏል። ስኳሩም በተመሳሳይ ሙሉ ለሙሉ መዳን ባይቻልም ለስኳር የሚወስዱትን የመድሃኒት መጠን መቀነስ ችለዋል። በአጠቃላይ እንደ ሰዎቹ ሁኔታ ለመዳን የሚወስድባቸው ጊዜ መርዘምና ማጠር ካልሆነ በስተቀር በአብዘኞቹ መድሃኒቶች ውጤታማ ናቸው፡፡

**በብርቱ ልፋት የተገኘ ማዕረግ**

የፈጠራ ባለቤት ሎሬት አለሙ መኮንን ሎሬት የሚለውን መጠሪያ ያገኙት ከአቢሲኒያ የሽልማት ድርጅት ነው። አቢሲኒያ የሽልማት ድርጅቱ በየዓመቱ በተለያየ ዘርፍ የተሰማሩ ትጉሃንን የሚሸልም ድርጅት ነው። ድርጅቱ በ2011 ዓ.ም ለትጉሃን የፈጠራ ሰዎችና አምራች ኢንዱስትሪዎች ዕውቅናና ሽልማት በሰጠበት ወቅት እርሳቸው በሠሯቸው የፈጠራ ሥራ የሎሬትነት ማዕረግ አግኝተዋል።

የሎሬትነት ማዕረግ ያገኙት ሎሬት አለሙ፤ በወቅቱ ብዙ ምርምርና ጥናት በማድረግ ያዘጋጁት መድሃኒትነት ያለው ተጨማሪ ምግብ ሰዎች ተጠቅመውት ውጤት ማምጣት መቻሉ ተረጋግጧል። መድሃኒቶቹም ለተለያዩ ህመሞች መፍትሔ መሆን የሚችሉ ተጨማሪ ምግቦች በመሆናቸው ጤናማ ማህበረሰብ ከመፍጠር አንጻር ያለው አበርክቶ፤ እንዲሁም በከፍተኛ ውጭ ምንዛሪ ወደ ሀገር ወቅስጥ የሚገቡ መድሃኒቶችን በመተካት ፋይዳው የጎላ መሆኑ ተመስክሮለታል፡፡

**መልዕክት**

ሀገር በቀል ዕውቀቶች ሀገራዊ ችግሮችን ከመፍታት አንጻር ጉልህ ሚና እንዳላቸው ይታመናል። የበርካታ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሀገር የሆነችው ኢትዮጵያም የብዙ ባህልና ሀገር በቀል ዕውቀቶች ባለጸጋ ናት። ይሁንና እነዚህ ለቁጥር የበዙ ሀገር በቀል ዕውቀቶች የተረሱ ቢመስሉም ኢትዮጵያውያን የሚያጋጥማቸውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን ሲፈቱበት ኖረዋል። አሁንም ለችግሮች ሁሉ ዘላቂ መፍትሔ መሆናቸው ይታመናል።

‹‹በአሁኑ ወቅት መንግሥት ለሀገር በቀል ዕውቀቶች ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ሲሆን፤ ይህም የፈጠራ ሥራ የሚሠሩትን እጅግ የሚያበረታታ ነው›› ያሉት ሎሬት አለሙ፤ አሁን ላይ ለሀገር በቀል ዕውቀት የተሰጠው ትኩረት ከዚህ ቀደም ያሳለፉኩትን ህመም አክሞልኛል። በማለት በተለይም በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ዶ/ር ተነሳሽነት በተቀመጠው የፖሊሲ አቅጣጫ ‹‹ሀገር በቀል ዕውቀቶች ለሀገር ኢኮኖሚ›› በሚል ለሀገር በቀል ዕውቀቶች ትኩረት ተሰጥቶ ባህላዊ ህክምናው በጤና ሚኒስቴር እውቅና መሰጠቱ የሚደነቅና የሚበረታታ ነው›› በማለት መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ሀገር በቀል እውቀቶች ጤናማ ማህበረሰብን ለመፍጠር የሚያግዙ በመሆናቸው ማህበረሰቡ መድሃኒቶቹን በቀላሉ አግኝቶ ጤናውን እንዲጠብቅ ይረዳዋል። በተለይም ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወጥቶባቸው ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ መድሃኒትና መድሃኒት ነክ የሆኑ ምርቶችን ሀገር በቀል በሆኑ ምርቶች በመተካት እንዲሁም በሥራ ዕድል ፈጠራና በኤክስፖርት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች ያሉት በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። የኛም መልዕክት ነው፡፡

# ባህልና ቱሪዝም

## የማይዳሰሱ ቅርሶችን የመጠበቅና የመንከባከብ ተጨባጭ ፋይዳ

**ዳግም ከበደ**

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ቅርስነት የተመዘገቡ የበርካታ መስህቦች ባለቤት ነች። ጥንታዊ ሥልጣኔና ሀገረ መንግሥት ያላት ቀደምትና የሰው ዘር መገኛ ጭምር ናት። በሀገሪቱ የአርኪዮሎጂ ፣ የፓሊዮንቶሎጂና ፓሊዮአንትሮፖሊጂ (መካነ ቅርሶች ጥናት) እንዲሁም የኢንታንጀብል (የማይዳሰሱ) ኢትኖግራፊ (የማህበረሰብ ባህል ጥናት) ቅርሶች ይገኛሉ። በታሪክ በባህል፣ በተፈጥሮ፣ በሥነ ፅሁፍ፣ በእምነት እንዲሁም በአያሌ ዘርፎች በአጭሩ ተዘርዝረው የማያልቁ የሰው ልጅ ሥልጣኔ አመላካች ሀብቶችን በውስጧ ይዛለች።

በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) የሚመዘገቡ ቅርሶች (መስህቦች) ሁለት አይነት መልክ እንዳላቸው የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ። እነዚህ ሀብቶች በሰው ልጅ ታሪክ፣ ሥልጣኔና ዛሬን የመድረስ ልህቀት ላይ እኩል ድርሻ እንደሚወስዱም ይገልፃሉ። የማይዳሰሱም ሆነ የሚዳሰሱ ቅርሶች በእኩል ደረጃ ሊጠበቁ፣ ሊለሙ ሊተዋወቁና የያዙት ፋይዳ ጎልቶ ሊወጣ እንደሚገባ እነዚሁ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

ኢትዮጵያ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶች (እንደ አክሱም፣ የፋሲል ግንብ፣ የጢያ ትክል ድንጋይ እንዲሁም የመስቀል፣ ጥምቀት፣ ኢሬቻ፣ የጨምባላላ የመሰሉ) ሀብቶች ያላት ቀደምትና ታሪካዊ ሀገር ነች። ቅርሶቹ የተነጣጠሉ ሳይሆኑ አንዳቸው ከአንዳቸው ጋር የሚመጋገቡ፣ አንዳቸው ለአንዳቸው በባህል እንዲሁም በእምነት የሚቆራኙ ሆነው እናገኛቸዋለን። ለምሳሌ ያህል በዩኔስኮ የዓለም ቅርስነት በማይዳሰስ የተመዘገበውን የመስቀል በዓል ብንመለከት በቀጥታ ከአክሱም፣ ከላሊበላ የሚዳሰሱ ቅርሶች ጋር የሚተሳሰር ሆኖ እናገኘዋለን። በመሆኑም ሃይማኖታዊና ባህላዊ እሴት የሆኑ የማይዳሰሱ ቅርሶችን ስንጠብቅ፣ ስናለማና ስናስተዋውቅ በተመሳሳይ የሚዳሰሱ ሀብቶቻችንም እኩል እንክብካቤና አስፈላጊውን ጥበቃ ማድረጋችንን ልንገነዘብ ይገባል።

በተመሳሳይ የማይዳሰሱ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ቅርሶች በራሳቸው ተዳሳሽ የሆነ እሴት እንዳላቸው ባለሙያዎች ይገልፃሉ። ይህንን እሴት ከሚወክሉት ውስጥ ደግሞ ባህላዊ አልባሳት፣ ምግቦች፣ ጌጣጌጦች እና መሰል ቁሳዊ ሀብቶች ይነሳሉ። ይህን ጉዳይ በዝርዝር ለመረዳት እንድንችል በጉዳዩ ላይ ሰፋ ያለ ዳሰሳዊ ጥናት ያደረጉ ተመራማሪን አነጋግረናል።

አቶ ደምረው ዳኜ በኢትዮጵያ ቅርስ ባለሥልጣን የኢንታንጀብልና የኢትኖግራፊ ቅርሶች ተመራማሪ ናቸው። የኢትዮጵያ ቅርሶች የምርምር ጉዞ በሚለው ዓመታዊ የምርምር ጉባዔ ላይ ‹‹በማይዳሰስ ቅርስ ውስጥ የሚገኝ የሚዳሰሱ እሴቶች እይታ›› /Exploring Tangible Values in the Intangible/ በሚል ርእስ ጥናታዊ ዳሰሳ አቅርበው ነበር። የዝግጅት ክፍላችን ይህንን ርእሰ ጉዳይ በዝርዝር ሊመለከተው ወድዷል።

አቶ ደምረው እንደሚሉት፤ የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርስ ስምምነት /the ICH Convention/ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርስ ጋር በተያያዘ በቀዳሚነት የተወሰደው እርምጃ እ.ኤ.አ በ1973 ቦሊቪያ በዓለም አቀፉ የኮፒራይት ኮንቬንሽን ውስጥ ፎክሎርን ለመጠበቅ የሚያስችል ፕሮቶኮል እንዲካተት ባቀረበችው ሃሳብ የተጀመረ መሆኑን ይናገራሉ። የቦሊቪያ ሃሳብ በጊዜው ስኬታማ ባይሆንም የማይዳሰስ ባህላዊ ቅርስ ልክ እንደ ተዳሳሽ (Tangible) ባህላዊ ቅርስ ትኩረት እንዲያገኝ ቀዳሚውን ግንዛቤ ለመፍጠር ያስቻለ መሆኑን ያስረዳሉ። ዩኔስኮ አንድ ዓመት ቀደም ብሎ እ.ኤ.አ በ1972 ታንጀብል የሆኑትን የባህልና የተፈጥሮ ቅርስ ጥበቃ ኮንቬንሽንን መቀበሉንም ይገልፃሉ።

የኢንታንጀብልና የኢትኖግራፊ ቅርሶች ተመራማሪው እንደሚሉት፤ ዩኔስኮ በማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርስ ጥበቃ ረገድ ቀዳሚ ሊባል የሚችለውን ርምጃ የወሰደው እ.ኤ.አ በ1982 መሆኑን ዋቢ መፅሀፍትን ጠቅሰው ያስረዳሉ። በዚህ ርምጃው ፎክሎርን ለመጠበቅ በሚል የኤክስፐርቶች ኮሚቴ ያቋቋመ መሆኑን አንስተው በድርጅቱ ውስጥ ቁሳዊ ያልሆኑ (የማይዳሰሱ) ቅርሶችን የሚከታተል የሥራ ክፍል /Section/ መመሥረቱን ያነሳሉ።

እንደ ተመራማሪው ገለፃ በ1982 በሜክሲኮ ከተማ የባህል ፖሊሲዎችን አስመልክቶ የተላለፈው ውሳኔ ባህል ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ አዲስና ሁለገብ ትርጉም መስጠቱ የሰው ልጅ ቅርስ መገለጫው ታንጀብል ቅርስ ብቻ ሳይሆን ኢንታንጀብል ቅርስ ጭምር መሆኑን ግልጽ ያደረገ መሆኑን ያስረዳሉ። ዩኔስኮም ባህል አንድ ህብረተሰብ ወይም ማህበራዊ ቡድን ከሌላው ተለይቶ የሚታወቅበትን ማንነቱን ለመግለጽ የሚያገለግሉት መንፈሳዊ፣ ቁሳዊ፣ ምሁራዊና ስሜታዊ ገፅታዎችን ሁሉ የሚያጠቃልል ሰፊ ፅንሰ ሃሳብ መሆኑን በዝርዝር ማስቀመጡን ያስረዳሉ። ከዚህም በላይ ባህል ሥነ ጥበብንና ሥነ ፅሁፋዊ ብቻ ሳይሆን የአኗኗር ዘይቤዎችን፣ የሰው ልጅ መሠረታዊ መብቶችን፣ የእሴት ሥርዓቶችን፣ ልማዶችንና እምነቶችን ጭምር የሚያካትት መስከ እንደሆነ በትርጓሜው ማስፈሩን ይናገራሉ፡፡

እ.ኤ.አ በ1997/98 የዘረጋው የሰው ልጅ አፋዊና ኢንታንጀብል ቅርስ ፕሮግራም (Proclamation of Masterpieces of Oral and Intangible Heritage of Humanity) አንዱና ተጠቃሽ ነበር የሚሉት አቶ ደምረው፤ በዚህ ፕሮግራም አማካኝነት የተወሰኑ እና የተለየ እሴት እንዳላቸው የታመነባቸውና ነገር ግን የመጥፋት አደጋ የተጋረጠባቸውን የአፋዊ እና የማይዳሰሱ ቅርሶች የሆኑ የባህል መገለጫዎችን ዝርዝር ለመመዝገብ መቻሉን ይናገራሉ።

**ከዓለም አቀፍ የቱሪዝም ገቢ 40 በመቶው ያህል ከማይዳሰሰው ባህላዊ ቅርስ ጋር በተያያዙ ከሚሰጡ አገልግሎቶችና ጉብኚቶች ይገኛል፤ በአጠቃላይ ሲታይ የቅርስ ጎብኝዎች ከሌሎች ጎብኚዎች የበለጠ ወጪ ያወጣሉ፤ ይህም በቀን ሲነጻጸር እስከ 38 በመቶ ያህል ብልጫ አለው። በተመሳሳይ የቅርስ ጎብኚዎች ረጅም ቆይታ የሚያደርጉ ሲሆን፣ ከተቀሩት ጎብኚዎች ጋር ሲነጻጸር 22 በመቶ ያህል ብልጫ አለው**

### ቅርሶቹን የመጠበቅና የመንከባከብ ፋይዳ

በኢትዮጵያ ውስጥ በማይዳሰሱ ቅርሶች ውስጥ ተካትተው የሚገኙ እሴቶችንም ሆነ በዓለማችን ላይ ያሉ የመስህብ ሀብቶችን መጠበቅና መንከባከብ በዓለም አቀፍ ሕግነት የተደነገገ መሆኑን የሚያነሱት ተመራማሪው፤ ይህም ቅርሶቹ በሚተገበሩዋቸው ማህበረሰቦችና ቡድኖች ውስጥ እየተተገበሩና ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፉ ህያው ሆነው መቀጠላቸው ማረጋገጥ እንደሚገባ ይናገራሉ።

‹‹የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶችን ከሚደርስባቸው ጥፋቶች ለመከላከል የተለያዩ ርምጃዎች እንዲወሰዱ ስምምነቱ ያስቀምጣል›› የሚሉት ተመራማሪው ከነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹ ቅርሶቹን መለየትና ያሉበትን ሁኔታ መረዳት፣ የቅርሶቹን አገልግሎትና ጠቀሜታ ለማስተዋወቅና ከጥፋት የመከላከያ ርምጃቸውን በእቅድና በፕሮግራም ውስጥ ለማካተት አጠቃላይ የመከላከያ /safeguarding/ ፖሊሲ ማዘጋጀት፣ ቅርሶቹን ከጥፋት የመከላከል ሥራ የሚሠራ ተገቢ ተቋም አካል ማቋቋም፤ ጥናትና ምርምሮችን ማበረታታትና ማካሄድ፣ ቅርሶቹን ከጥፋት ለመከላከል የሚያግዙ ሌሎች የሕግ ፣ የቴክኒክ የአስተዳደርና የፋይናንስ ርምጃዎችን ማለትም ለማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች ማኔጅመንትና አስተላልፎ የሚያግዙ ማሠልጠኛዎችን መመስረት፣ ቅርሶችን ለመድረስ ወይም ለማየት የተቀመጡ ባህላዊ ክንውኖችን ሳይጣሱ ለእይታ ማቅረበ መሆኑ ይናገራሉ።

### የማይዳሰሱ ቅርሶች ፋይዳ

ተመራማሪው ኢትዮጵያ በማይዳሰሱ የሰው ልጅ ወካይ ቅርሶችን ዝርዝር ውስጥ የሚካተቱ ሀብቶቿን መጠበቅና በመንከባከብ በርካታ ፋይዳዎች ማግኘት እንደምትችል ይገልፃሉ። የመጀመሪያው ባህላዊ ቅርስ የሚገኘው ተጨባጭ እሴት ቅርሱን ወደ ቁስ ወይም ምርት በመለወጥ የሚገኝ ጠቀሜታ መሆኑን ያስረዳሉ። በዚህም ባህላዊ እሴቶችን የሚያንፀባርቁ እሴቶችን ወደ ምርትና ቁስነት በመቀየር ለጎብኚዎች በማቅረብ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን ማስገኘት እንደሚቻል ያስረዳሉ። በምሳሌነትም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ባህላዊ ምግቦች፣ አልባሳት እና የማህበረሰቦችን እሴቶች መገለጫ የሆኑ ጌጣጌጦች ያነሳሉ። እነዚህ ቁሳቁሶች ከመገለጫነት አልፈው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸውም ጉልህ መሆኑን ይናገራሉ።

ከዓለም አቀፍ የቱሪዝም ገቢ 40 በመቶው ያክል ከማይዳሰሰው ባህላዊ ቅርስ ጋር በተያያዙ ከሚሰጡ አገልጎሎችና ጉብኝቶች እደሚገኝ በማስረጃነት የሚጠቅሱት አቶ ደምረው፤ በአጠቃላይ የቅርስ ጎብኚዎች /Heritage tourist/ ከሌሎች ቱሪስቶች የበለጠ ወጪ እደሚያወጡ እና በቀን ሲነጻጸርም እስከ 38 በመቶ ያክል የበለጠ መሆኑን ያስረዳሉ፣ በተመሳሳይ የቅርስ ጎብኚዎች /Heritage tourist/ ረጅም ቆይታ 22 በመቶ ያክል የበለጠ ቆይታ እደሚያደርጉ መረጃዎችን ጥቅሰው ያስረዳሉ። ይህም ማለት ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎች የዓለማችን ሀገራት ቅርሶቻቸውን መንከባከባቸውና ማስተዋወቃቸው ዳጎስ ያለ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንደሚያስገኝላቸው ያስረዳሉ።

በኢትዮጵያ በተለይ በትግራይ ክልል ቀደም ሲል የማይዳሰሱ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ቅርስ የሚጎበኙ ቱሪስቶች ቁጥር አስመልክቶ የተጠና አንድ ጥናትን ዋቢ በማድረግ ተመራማሪው እንደሚያስረዱት፤ በአሸንዳ 105 ሺህ ያክል ቱሪስት እንደሚጎበኘው፣ አክሱም ጽዮንን 95 ሺህ ያክል ቱሪስት እንደሚጎበኘው፣ የመስቀል በዓል አከባበርን 40 ሺህ ያክል ቱሪስት እንደሚጎበኘውና ጥምቀትን 10 ሺህ ያክል ቱሪስት እንደሚጎበኘው ይገልፃሉ። ከዚህ መነሻ ብቻም የእሴቶቹን መጠበቅና መንከባከብ በእጅጉ አያሌ ጠቀሜታዎች እንደሚያስገኝ መረዳት ቀላል መሆኑን ይናገራሉ።

‹‹ትግራይን ከሚጎበኘው የውጭ እና የሀገር ውስጥ ቱሪስት 60 በመቶ በመቶ ያክሉ ኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርስን እንደሚጎበኝ መረጃው ያመለክታል›› በማለት በምሳሌነት የሚያነሱት ተመራማሪው ከዚህ ቁጥር ተነስተን እያንዳንዱ ቱሪስት በአማካኝ በተለያዩ አገልግሎቶች የሚያወጣውን ትራንስፖርት፣ ምግብ፣ ማረፊያ፣ መዝናኛ ወዘተ ተርፈ ማስላት ብንችል ትልቅ ዋጋ ያለው ተጨባጭ ፋይዳዎችን እንደሚያስገኝ መገመት አያዳግትም ይላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የትውፊታዊ የእደጥበብ ሥራ ክህሎት ውጤቶች የሆኑትን ልዩ ልዩ የእደጥበባት ምርቶችን፣ የሸማ ሥራ፣ የአለላ ወይም የሰፌድ ሥራ፣ የነሀስ፣ የብርና የወርቅ ወዘተ ጌጣጌጦች ሥራን፣ የፈረስ ጭራ፣ የቆዳ እና የመሳሰሉትን ትውፊታዊ እደጥበብ ሥራ እውቀቶችን ወደ ሀብት በመለወጥ ለገበያ በማቅረብ የሚገኘው ትሩፋት ወይም ሀብት ሌላኛው የማይዳሰስ ባህላዊ ቅርሶች የሚያስገኙት ተዳሳሽ እሴት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

የኢንታንጀብልና የኢትኖግራፊ ቅርሶች ተመራማሪ አቶ ደምረው በማጠቃለያ ሃሳባቸው እንደገሚገልፁት፤ ከእያንዳንዱ የሚዳሰስ ቅርስ የማይዳሰስ ቅርስ አለ። በመሠረቱ የሚዳሰሰውን ቅርሱን የፈጠረው የማይዳሰስ በምንለው ምድብ ውስጥ የሚያርፈው እውቀትና ክህሎት ነው። ስለ አክሱም ሀውልት ግዝፈት ወይም ስለላሊበላ ውቅር አብያተክርስቲያናት ሲታሰብ ‹‹እንዴት አድርገው ጠረቡት፣ ቀረጹት ወይ ደግሞ አቆሙት›› ብለን እናሰላስላለን የሚሉት ተመራማሪው፤ ከፊታችን የቆመውን ሀውልት ወይም ውቅር አብያተክርስቲያን የሠራው የዛን ዘመን የማይዳሰሰውን ፍልስፍና መሆኑን መገንዘብ እንደሚኖርብን ያስረዳሉ። በዚህም የተነሳ ለአሠራርና ለመግባባት ካልሆነ በስተቀር ሁለቱን ነጥሎ ማየት እንደማይቻልም ይገልፃሉ።

እንደ ተመራማሪው ሃሳብ፤ የማይዳሰስ ባህላዊ ቅርስ በራሱ የሚዳሰስ ወይም ተጨባጭ የሆኑ ውጤቶች ወይም ፋይዳዎችን ያስገኛል። በመጀመሪያ የማይዳሰሱ የሚባሉትን መመዝገብና መለየት ሲቻል፣ ማጥናትና ምርምር ማድረግ ሲጀመር ወደ ሚዳሰስ እሴትነት መለወጥ እንደሚጀመር መታወቅ እንዳለበት ያስረዳሉ። በመሆኑም የማይዳሰስ ባህላዊ ቅርሱን በዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት ጠብቆ ለትውልድ ለማስተላለፍ ትርጉም ያለውና ተጨባጭ ጥቅም መስጠት ወደሚችልበት ሁኔታ መለወጥ ይገባል ሲሉ ምክረ ሃሳብ ይሰጣሉ፤ ለተግባራዊነቱም ተባብሮ መሥራት እንደሚገባ አሳስበዋል።

# ሳምንቱን በታሪክ

## የመጨረሻው የኢትዮጵያ ንጉሥ

ዋስልኝ አየለ

ኢትዮጵያ ልክ እንደ አውሮፓና ሌሎች የዓለም ሀገራት ሁሉ ለሺህ ዘመናት በንጉሣዊ ሥርዓት ስትተዳደር ቆይታለች። በእነዚህ ነገሥታቶቿ የኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት እና የሀገር ግንባታ የተለያየ ቅርጽ ሲይዝ ቆይቷል። በእነዚህ ነገሥታቶቿ ታፍራና ተከብራ፣ ሉዓላዊነቷን አስጠብቃ ኖራለች።

በዘመን ሂደት ዓለም አዲስ ቅርጽ እየያዘች መጣች። ንጉሣዊ ሥርዓት ዘመን ሊሽረው ግድ ሆነ። ባላባት እና ገባር የሚባል ነገር ዘመኑን የማይመጥን ኋላቀር ሆነ። የሰው ልጅ ዝግመተ ለውጣዊ ሂደት የተለያዩ ዕድሳቶችን እየያዘ ይሄዳልና የአኗኗር ዘይቤውን ከዋሻ ወደ ቤት መሥራት፣ ከአደን ወደ እርሻና ሌሎች ሥራዎች እንደተለወጠው ሁሉ የአስተዳደር ሥርዓቱንም በዚያው ልክ እያሻሻለ፣ መብቱን እየጠየቀ መምጣት ላይ ደረሰ። በመሆኑም የፊውዳል ሥርዓት በቃህ ተባለ።

በዓለም የተፈጠረው አብዮት ጊዜውን ጠብቆ ወደ ኢትዮጵያ መጣና ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴን በታሪክ የኢትዮጵያ የመጨረሻው ንጉሥ አደረገ። የንጉሣዊ ሥርዓት ታሪክ ሲነሳ ቀድሞ የሚነሳው ስም የቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ይሆናል ማለት ነው። ምክንያቱም የመጨረሻው ንጉሥ ናቸው። ሌሎች ነገሥታት እንደየታሪክ አጋጣሚያቸው የሚነሱበት ምክንያት ብዙ ቢሆንም በንጉሣዊ ሥርዓት ታሪክ ግን ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ «የመጨረሻው» እየተባሉ ይነሳሉ። ወዲህ ደግሞ ረጅም ዘመናት የገዙ እና ረጅም ዕድሜ የኖሩም መሆናቸው ንጉሣዊ ሥርዓትን ያጎላዋል።

በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን በኢትዮጵያ የነገሥታት ታሪክ የመጨረሻው ንጉሥ የሆኑት ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ የተወለዱበትን ሐምሌ 16 ቀን ምክንያት በማድረግ እናስታውሳቸዋለን። ከዚያ በፊት እንደተለመደው ሌሎች የዚህ ሳምንት ክስተቶችን በአጭር በአጭሩ እናስታውስ።

ከ24 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሐምሌ 16 ቀን 1992 ዓ.ም የበርካታ የታሪክ መጻሕፍት ጸሐፊው አቶ ተክለፃድቅ መኩሪያ አረፉ። የቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴን ጨምሮ የኢትዮጵያን ነገሥታት ታሪክ የጻፉት ተክለጻድቅ መኩሪያ ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ በተወለዱበት ቀን አረፈዋልና ታሪካቸው በአንድ ቀን ሊታወስ ይችላል።

ከ60 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሐምሌ 18 ቀን 1956 ዓ.ም ከአፖሎ 11 መንኮራኩር ጋር ወደ ጨረቃ ተወስዶ የነበረው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከጨረቃ ከመጣው ድንጋይ እንዲሁም ከአሜሪካው ፕሬዚደንት ሪቻርድ ኒክሰን መልዕክት ጋር ለንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ተበረከተ። ሰንደቅ ዓላማውንና ድንጋዩን ከመልዕክቱ ጋር ለንጉሠ ነገሥቱ ያስረከቡት በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ነበሩ።

ከ108 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሐምሌ 20 ቀን 1908 ዓ.ም የንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ እና የእቴጌ መነን አስፋው ልጅ የሆኑትና የወሎ ጠቅላይ ግዛት ገዢ የነበሩት ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋወሰን ኃይለሥላሴ ተወለዱ።


ከ147 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሐምሌ 20 ቀን 1869 ዓ.ም ስመጥር የሙዚቃ ባለሙያ፣ ባለቅኔ፣ ቀራፂ፣ ሠዓሊ፣ ነጋዴ፣ መኪና አሽከርካሪ፣ መካኒክ፣ ፖለቲከኛ፣ ፎቶ አንሺ... በአጠቃላይ የበርካታ ሙያዎችና ተሰጥኦዎች ባለቤት የነበሩት ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ ተወለዱ።

ከ44 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሐምሌ 20 ቀን 1972 ዓ.ም ኢትዮጵያዊው አትሌት ሻምበል ምሩፅ ይፍጠር የሞስኮ ኦሊምፒክ የ10 ሺህ ሜትር የሩጫ ውድድርን በማሸነፍ ኢትዮጵያን የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት አደረገ።

ከ28 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሐምሌ 21 ቀን 1988 ዓ.ም ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ፋጡማ ሮባ በአትላንታ ኦሊምፒክ የሴቶች የማራቶን ውድድርን በማሸነፍ ኢትዮጵያን የወርቅ ሜዳሊያ ባለቤት ማድረግና በሴቶች የኦሊምፒክ ማራቶን ውድድርን ያሸነፈች የመጀመሪያ አፍሪካዊት መሆን ቻለች።

አሁን በዝርዝር ወደምናየው የኢትዮጵያ የመጨረሻው ንጉሥ ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ታሪክ እንሂድ።

ከ132 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሐምሌ 16 ቀን 1884 ዓ.ም፤ ኢትዮጵያን ከ1910 ዓ.ም እስከ 1921 ዓ.ም በአልጋ ወራሽነትና በንጉሥነት፣ ከጥቅምት 23 ቀን 1923 ዓ.ም እስከ መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም ድረስ በንጉሠ ነገሥትነት የመሩት ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ተወለዱ።



**ተፈሪ መኮንን (በኋላ ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ)**

አጼ ኃይለሥላሴ የመጨረሻው ንጉሥ ብቻ ሳይሆን የመጨረሻው የሰለሞናዊ ሥርዎ መንግሥት ንጉሠ ነገሥትም ያደርጋቸዋል። ምክንያቱም ከ13ኛው ክፍለ ዘመን በፊት የነበሩት ሥርዎ መንግሥታት ሌላ ነበሩ። ሰለሞናዊ ሥርዎ መንግሥት ከ13ኛው ክፍለ ዘመን (1270) እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን (1967 ዓ.ም) ድረስ ለ700 ዓመታት አካባቢ የኖረ ነው።

ሰለሞናዊ ሥርዎ መንግሥት ከኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ሳባ እና ከእስራኤሉ ንጉሥ ሰለሞን ከተገኘው ቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ እንደሆነ በአፈ ታሪክም በጽሑፍ ታሪክም ይነገራል። ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ የነገሡ ነገሥታትም ራሳቸውን የሰለሞናዊ ሥርዎ መንግሥት ቤተሰብ አድርገው ነበር ቅብዓ መንግሥት የሚያገኙት። ይህ ሥርዎ መንግሥት በኢትዮጵያ ለ700 ዓመታት ያህል ሲያገለግል ኖሮ፤ በኢትዮጵያ በተቀሰቀሰ አብዮት በወታደራዊው ደርግ ፍጻሜውን አግኝቷል። ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴም የሰለሞናዊ ሥርዎ መንግሥት የመጨረሻው ንጉሥ ተብለው በታሪክ እንዲቀመጡ ሆኗል።

የምናስታውሳቸው የልጅነት ታሪካቸውን «ሕይወቴ እና የኢትዮጵያ ርምጃ» ከተሰኘው ከራሳቸው መጽሐፍ፣ አስተዳደራዊ ታሪካቸውን «የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983» ከተሰኘው የፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ መጽሐፍ፣ ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ እና ከተለያዩ ድረ ገጾች ባገኘነው መረጃ ነው።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ (የያኔው ተፈሪ) ሐምሌ 16 ቀን 1884 ዓ.ም ከሐረር ከተማ 30 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በምትገኘው ኤጀርሳ ጎሮ በተባለች ቦታ ተወለዱ። ሕጻኑ ተፈሪ ከራስ መኮንን ወልደሚካኤል እና ከወይዘሮ የሺእመቤት ዓሊ ጋምቾ ከሐረር ከተማ 30 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ኤጀርሳ ጎሮ በተባለች ቦታ ነው የተወለደው።

አባታቸው የአጼ ምኒልክ የአክስት ልጅ ናቸው። እናታቸው ወይዘሮ የሺእመቤት ዓሊ ከተፈሪ በፊት ስድስት ልጆች ወልደው የነበረ ቢሆንም፤ ሁሉም እንደተወለዱ ሞተውባቸዋል። አሁንም ሰባተኛውን ልጅ ተፈሪን ለመውለድ ሁለት ወራት ቀርቶኛል ብለው ሲያስሱ ድንገት በከባድ ምጥ ይያዙና ፈጣኑ ተፈሪ በተረገዙ በሰባተኛው ወር ይወለዳሉ።

ልጅ ተፈሪ እንደተወለዱ ቤተዘመድ «እናቱ ካዩት እንደተለመደው ይሞታል» በማለት ህፃኑን እናቱ ሳያዩት ይዘውት ይሄዳሉ። ይህ ክስተት በባህላዊ አገላለፅ «ሾተላይ» የሚባል ሲሆን፤ ሰው ላይ ሊኖር የሚችለው ኃይለኛ የዓይን ጨረር ሌላ ሰው ላይ ሲያርፍ እስከሞት የሚያደርስ ጉዳት እንደሚያስከትል ይታመናል። በሳይንሳዊ ገለፃ ደግሞ የእናት ወይም የአባት የደም አይነት «RH Negative» ሆኖ የሌላኛው RH Positive ይሆንና የሁለቱ ወላጆች ደም ሳይጣጣም ሲቀር የሚከሰት ችግር ተደርጎ ይገለፃል።

በዚህ ምክንያት ህፃኑ ተፈሪ ከእናቱ ወዲያው መለየት ነበረበትና ከወላጆቹ ቤት ወጥቶ ዘመድ ቤት ማደግ ይጀምራል። እናቱ የህፃኑን ሁኔታ በመልዕክት ሲከታተሉ ከቆዩ በኋላ፤ በድጋሚ አርግዘው ነበርና ከ20 ወራት በኋላ መጋቢት 6 ቀን 1886 ዓ.ም በዚሁ በወሊድ ምክንያት ሕይወታቸው አለፈ። ልጅ ተፈሪ የእናትን ጣዕም ሳያውቀው ቀረ። ከህፃንነቱ ጀምሮ የአጎቱ የደጃዝማች ብሩ ኃይለማርያም ባለቤት ወይዘሮ ትሰሜ አባይርጋ ከእምሩና ከልጃቸው ጋር አሳደጉት።

በዚያም ሳሉ አባታቸው ራስ መኮንን የፈረንሣይኛ ትምህርት እንዲማሩ መምህር ቀጠሩላቸውና ልጅ ተፈሪ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ አደጉ። በ10 ዓመታቸው በ1894 ዓ.ም ከሐረር ወደ አዲስ አበባ መጥተው ለመጀመሪያ ጊዜ ከአጼ ምኒልክ ጋር ተገናኝተው ተዋውቀው ተመልሰው ወደ ሐረር ሄዱ።

አባታቸው ራስ መኮንን በ1898 ዓ.ም ህዳር 10 ቀን የደጃዝማችነት ማዕረግ ሰጥተው «ጋራ ሙለታ» የተባለውን አውራጃ ሾሟቸው። «ተከታይ ልጄ ደጃዝማች ተፈሪ ነው» ብለውም ለመኳንንቶቻቸው ይፋ አደረጉ። ልጅ ተፈሪ በ14 ዓመታቸው የደጃዝማችነት ማዕረግ እንዳገኙ ወዲያው በ1898 ዓ.ም መጋቢት 13 ቀን አባታቸው ራስ መኮንን አረፉ።

በዚህ ጊዜ ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ተፈሪን ከሐረር ወደ አዲስ አበባ አስመጥተው ደጃዝማችነታቸው እንደፀና ቀረብ የሚለውን የሰላሌን ግዛት ሾሟቸው። ተፈሪ ግን ለተሰጣቸው ግዛት ሌላ እንደራሴ ወክለው በኢትዮጵያ ብቸኛ ትምህርት ቤት በነበረው በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ገብተው ሐረር እያሉ የጀመሩትን ትምህርታቸውን ቀጠሉበት።

ከዚያም በ1899 ዓ.ም የባሶ በጌምድር ግዛትን፤ ቀጥሎ በ1900 ዓ.ም ሲዳሞን ተሾሙ። ከሁለት ዓመት በኋላም ሲዳሞን ትተው የአባታቸውን ግዛት ሰፊውን ሐረርጌንና አውራጃዋን እንዲያስተዳድሩ ተደረገ። የሐረርጌ ሕዝብም በደስታ ተቀበላቸው። በ1903 ዓ.ም በዚሁ በሐምሌ ወር የንጉሥ ሚካኤልን የልጅ ልጅ ወይዘሮ መነንን አግብተው መኖር ጀመሩ።

ደጃዝማች ተፈሪ በ19 ዓመታቸው ወይዘሮ መነንን አግብተው፣ በ1905 ዓ.ም የመጀመሪያ ልጃቸውን ልዕልት ተናኘወርቅን ወለዱ። ከዳግማዊ ምኒልክ ሞት በኋላ ሥልጣን የያዙት ልጅ እያሡ በ1907 ዓ.ም ደጃዝማች ተፈሪን ከሐረርጌ ግዛት ሽሯቸው ወደ አዲስ አበባ መጥተው እንዲቀመጡ ተደረገና ወዲያው የከፋን ግዛት ሾማቸው። ሆኖም ደጃዝማች ተፈሪ አልሄዱበትም። ተፈሪ የአውሮፓ ቋንቋ የሚያውቁ፣ ከአውሮፓውያኑ ጋር ያለአስተርጓሚ በቀጥታ የሚነጋገሩ ጨዋ፣ ዝምተኛ ... እየተባሉ ቆዩ።

በ1909 ዓ.ም አቤቶ ልጅ እያሱ ከሥልጣን ተወግዶ ዘውዲቱ ሲነግሡም በወቅቱ አዲስ አበባ የነበሩት ደጃዝማች ተፈሪ፣ «ራስ» በሚል ማዕረግ አልጋወራሽ ሆነው የራስ ወርቅ አሠሩ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ንጉሠ ነገሥት እስከሆኑበት እስከ 1923 ዓ.ም ድረስ በተከታታይ ልዑል አስፋወሰንን፣ ልዕልት ዘነበወርቅን፣ ልዕልት ፀሐይን፣ ልዑል መኮንንን እና ልዑል ሳህለሥላሴን ወልደዋል።

ንጉሡ እንደሚሉት፤ በልጅነታቸው እንደ ቀደሙት ነገሥታት ልጆች በቅምጥል ሳይሆን እንደ ተራ ግለሰብ ልጆች ነው ያደጉት። የእርሳቸው ልጆች ግን በቅምጥል እንዳደጉ በሌሎች ወገኖች የተጻፉና የሚነገሩ ታሪኮች ያሳያሉ።

በብዙ ውጣ ውረድ ያለፈው የተፈሪ ሕይወት አሁን ወደ ንጉሠ ነገሥትነት እየመጣ ነው። መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም ልጅ ኢያሱ ከሥልጣን ተሽረው ዘውዲቷ ምኒልክ (የዳግማዊ አጼ ምኒልክ ልጅ) ንግሥት ሲሆኑ፤ ተፈሪ ደግሞ አልጋ ወራሽ ሆኑ። ከዚያ በኋላ «እጅግ በጣም ውስብስብ ነበር» በሚባል አካሄድ ጥቅምት 23 ቀን 1923 ዓ.ም «ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ስዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ» ተብለው ለ44 ዓመታት ነገሡ። ይህ ታሪካቸውም የመጨረሻው ንጉሥ ብቻ ሳይሆን ረጅም ዓመት (ለግማሽ ክፍለ ዘመን የተጠጋ) ያስተዳደረ ንጉሥ እንዲሆኑም አድርጓቸዋል። አንዳንድ የታሪክ ተንታኞችም ለንጉሣዊ ሥርዓት መውደቅ ምክንያት የሆነው የእርሳቸው እስከ እርጅና ዘመን ሙጭጭ ማለት ነው እንዲሉ አድርጓል።

ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርትን በማስፋፋት ይመሰገናሉ። ለዘመናዊ ትምህርትም ብዙ ተማሪዎች ወደ አውሮፓ ተልከዋል። እነዚህ በንጉሡ ጊዜ የተላኩ ተማሪዎች ሀገራቸውን ከሠለጠኑት ሀገራት ጋር በማወዳደር የንጉሡን ሥርዓት አምርረው መጥላትና መቃወም ጀመሩ። ይህን ለመግለጽ ይመስላል ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ በመጽሐፋቸው መግቢያ ላይ ስለዘመናዊ ትምህርት የሚከተለውን ብለዋል።

«.. በንጉሠ ነገሥትነት አደራ ከተቀበልንበት ከ፲፱፻፲፱ ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን ያገሩን ውስጥ ሥራ በየጥቂቱ ለማሻሻል፤ የምዕራባውያንንም የሥልጣኔ ሥራ ባገር ውስጥ አስገብተን ሕዝባችን ወደ ትልቅ ደረጃ የሚደርስበትን በሚቻለን ሁሉ ጀምረናልና ሕሊናችን አይወቅሰንም።

በየጥቂቱ ማለት ሕፃንን ልጅ በማባበልና በማስለመድ ካልሆነ በቀር በእጁ የያዘውን ነጥቆ ቢወስዱበት ደስ አይለውም ። በማሳየትና በማቅመስም ካልሆነ ማናቸውንም ምግብ ቢሰጡት ሊመገበው አይፈቅድም ። ጥርስም እስቲያበቅል ወተት ወይም ሌላ ለስላሳ ምግብ ካልመገቡት ዳቦ ወይም ሥጋ ቢያቀርቡለት ሊመገበው አይችልም።

እንደዚሁም በትምህርት ቤት ሳይማርና በጆሮውም የዕውቀትን ነገር ሳይሰማ በዓይኑም ሳይመለከትና ሳይመረምር በልማድ ብቻ የሚኖረውን ሕዝብ ብዙ ዘመን የኖረበትን ልማዱን በትምህርት አስለቅቆ አዲስ ልማድ እንዲቀበል ለማድረግ በመቸኰልና በጭካኔ ሥራ ሳይሆን በትዕግሥትና በትምህርት በየጥቂቱ በቀን ብዛት ማስለመድ ያስፈልጋል ማለት ነው።»

ከዚህ መግቢያ ሥር «የካቲት ፲፱፻፳፱ ዓ.ም ተጻፈ።» ይላል። 1929 ዓ.ም ገና አብዮቱ ያልተጀመረበት ነው። በተለምዶ የ60ዎቹ ትውልድ የሚባሉ አብዮተኞች የውጭ ትምህርትን በአንድ ጊዜ ካልተጋትን በማለታቸው ይወቀሳሉ። ንጉሡ የምዕራባውያንንም ሆነ የምሥራቃውያኑን ትምህርት በአንድ ጊዜ መጋት ትክክል እንደማይሆን ቀድመው አስበው ነበር ማለት ነው። ምክንያቱም ለረጅም ዘመን በልማዳዊ አኗኗር የኖረ ማህበረሰብ አንድ ጊዜ የሌላ ሀገር ባህል ቢጭኑበት ውጤታማ አይሆንም።

ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ የቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሤን ንግሥና እና ጥቅል መለያ ርዕዮት ከገለጹባቸው አንቀጾች የሚከተለውን ቃል በቃል እናስቀምጥ።

«... የተፈሪ የፖለቲካ ቁመና መለወጥ የጀመረው ግን ገና ንጉሠ ነገሥት ከመሆኑ በፊት ነው። በ1921 ዓ.ም ንጉሥ ከተባለ ወዲህ ጋዜጦችም የቀድሞ ነፃታቸው እየኰሰሰ ተፈሪን ማወደስ ጀምረዋል። ሥርዓተ ንግሡ የተፈጸመበት ጥምት 23፣ 1923 የሂደቱ ማሳረጊያ እንጂ መጀመሪያ አልነበረም። እንደዚህ ፍጹማዊ ሥልጣን ከጨበጠ በኋላ የዘመነ መሳፍንት ቅሪቶችን የማስወገዱን ጉዳይ ሥራዬ ብሎ ተያያዘው። ቴዎድሮስ አሐዳዊ መንግሥት ለመመሥረት ሞክሮ እንደከሸፈበት ይተናል። ዮሐንስና ምኒልክም ከዚህ ትምህርት ወስደው ነው ይመስላል ከክልላዊ አገዛዝ ጋር ታርቆ መኖርን መርጠዋል። የተናቁትንና የተጠሉትን አቀርባለሁ የሚለው ለጊዜው እንግዳ የሆነው የኢያሱ ሙከራም ዙፋኑን እስከማጣት አብቅቶታል። ከዚህ ሁሉ አንፃር ኃይለ ሥላሴ በታሪክ ከሚታወቅባቸው ነገሮች አንዱ ቴዎድሮስ ያለመውን አሐዳዊ መንግሥት እውን ማድረጉ ነው። ይህም ሁኔታ ነው ከሕይወት ታሪኩ (ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ) እንደምንረዳው ንጉሠ ነገሥቱ ራሱን እንደ ፀረ ፊውዳል ታጋይ እንዲቆጥር ያደረገው። ይህም የፊውሊዝምን መሠረታዊ ኢኮኖሚያዊ ይዘት ካለማጤን የመጣ አስተሳሰብ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ኃይለ ሥላሴ ይታገል የነበረው ፊውዳሊዝምን ለማስወገድ ሳይሆን ባንድ ወገን የንጉሡን ሥልጣን አጠናክሮ በሌላ ወገን ደግሞ የመሳፍንቱን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም አስከብሮ ፊውዳሊዝምን በአዲስ መሠረት ላይ ለማቆም ነው። በኢትዮጵያ የፍጹማዊ አገዛዝ ዓይነተኛ ባሕርይም ይኸው ሆነ።»

ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ጥቅምት 23 ንግሥናቸውን አውጀው ከስምንት ወራት በኋላ ሐምሌ 9 ቀን 1923 ዓ.ም የመጀመሪያውን የተጻፈ ሕገ መንግሥት አውጀዋል። ያም ሆኖ ግን እየዋለ እያደረ ሲሄድ የንጉሡ ሥርዓት ውጫዊና ውስጣዊ ጫና በዛበት። በተለይም ከ1953ቱ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላ «የመሬት ለአራሹ» ጥያቄ አድጎ አብዮቱ ተቀጣጠለ። በመጨረሻም 1966 ዓ.ም ንጉሣዊ ሥርዓቱ ያለቀለት መሆኑ ታወቀ። መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም ለ44 ዓመታት ያህል የኖረው የቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥትነት፣ በኢትዮጵያ ለሺህ ዘመናት የኖረው ንጉሣዊ ሥርዓት ሙሉ ለሙሉ አከተመ። እነሆ ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴም በኢትዮጵያ ታሪክ የመጨረሻው ንጉሥ ሆኑ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

## ጉዱ ሲራክ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

መገን በአራዳ! መገን በወሎ! ምን ቢሉ ምን ይታጣል... ከወሎ የወጣ ከአራዳ ያልታጣ መገኑ በፍቅር ነው። የገራገርዋን እናት ጡት ጠብቶ፣ በሼህ ሁሴን አድባር ተመርቆ፣ በአንቱ ከራማ የተባለለት ደርሶ ጥበብ ይዘራል። ወጪቱን ከጎተራው ይሞላል። ገራገሯ መቼስ ማኅፀኗም ጥበብ አብቃይ፣ የጥበብ ማደሪያ ነው። ከዚያም ተወልደው፣ ከወሎ ሳር ቅጠል ምሰው፣ ለምለሙን ለጥበብ ቤት ከነሰነሱት መሀከልም አንዱ ሲራክ ታደሰ ነው።

ዛጎል ባለጥበብ አምባር እንቁ ጌጥ በጥበበ ኢትዮጵያ ቤት ውስጥ የሠራው ታይቷል። የዘራውም በቅሏል። ከዚህቹ ጥበብ በዓይነት በዓይነቷ ዘግኖ ከየአውድማው ላይ ሲዘራ ሲያበቅል ኖሯል። ደርሶ አዝመራው አሽቶ “እሸት በላሁኝ” ያላለ ማን አለ... ሲራክ ተዋናይ ነው ሲሉ በወዲያኛው አጥር ዘሎ ገጣሚ ይሆናል። ደግሞ ገጣሚ ነው ሲሉት ሰከም ሰከም እያለ በጥሻው ጋራውን ዞሮ ከምንጩ ውሃ ፉት ብሎ ከወዲያኛው መስክ ይታያል።

እናም ሲራክ ታደሰ የሙዚቃ ዜማ እየደረሰ ዝነኞቹን ሁሉ ባለህምራዊ ዜማ ሲያደርጋቸው ውሎ ያድራል በማለት ወሬውን ከወዲያ ወዲህ አዳረሱት። የለም ሳናይስ አናምንም እያሉ ዱካውን ተከትለው የሄዱም “እንዴት ያለው እሳተ ጎመራ ነው እቴ!” እያሉ እጃቸውን በአፋቸው ጭነው ጉድ! ሲሉ ተመለሱ። “አሁንስ በቃ አወቅነው ሲራክ ማለት ተዋናይ፣ ገጣሚና የዜማ ደራሲ ነው” ሲሉ አወቅን ተዋወቅን ብለው በአራት ነጥብ ዘጉት። እሱ ግን የዘገናት ጥበብ እንደቆሎ ተበትና የምታልቅ ሳትሆን ሿ! እያለ ውሎ ፏ! እያለ እንደሚያድረው የዓባይ ፏፏቴ ማክተሚያ አልነበረውም።

የኋላ ኋላም ሲራክ ታደሰ ኮሜዲያንም ሆነ የሚል ሌላ ያልተሰማ ወሬ ከየጆሮው ውስጥ ጥልቅ አለ። “ጉልሽ? ኧረ እስቲ አሁንስ የሆንከውን ንገረን። እዚህቹ ካላየን በስተቀር የለም አናምንህም። ኮሜዲያን ሆንክ አሉ። በል አሳየንና እኛም እንመንህ” ቢሉ፤ ለመስማት የቋመጠውን በሳቅ ፈጃቸውና “እኔ ማለት እንግዲህ እንዲህ ነኝ” አላቸው። አመኑት። በሳቅ ተለኩሰውም እያደነቁት ብቻ ተነስተው ሄዱ። ይኼን “ጉልሽ” የሚል ስያሜ ያገኘው እንዲሁ በዘፈቀደ አልነበረም።

በ”አምታታው በከተማ” ቲያትር ላይ ጉልሽን ሆኖ ሲጫወት እጅግ ተወዳጅና ተናፋቂ እስኪሆን ድረስ ብቃቱን ለጉድ አስመለከተና በዚያው ስሟን ይዞ ሹልክ አለ። ከዚያ ወዲያም “ጉልሽ...ጉልሽ” ሆነ መጠሪያው።

ታዲያም ሲራክ ታደሰ ቢሉ፣ “ጉልሽ” እያሉ በሰጡት ተቀጽላ ስሙ እየጠሩ፣ እሱ ማለት ሲሉ አምስት የጥበብ ዛጎላማ አትሮኖሶችን የያዘ ሁሉ ጥበብሽ የሆነ ሰው ነው። በትወናው የቲያትር መድረክ ላይ ሳይቀር ልኩን አሳይቶ በቁም አስጨብጭቧል። ከወጣባት የሙዚቃ ፊላ ስር እንደተቀመጠ መጥቶ ያልጎበኘው እውቅ ድምጻዊ አልነበረም። ግጥም ጻፈ። ዜማም ደረሰ። በቀልዱም እየተኮማኮመ ወደ ታዋቂዎቹ የኮሜዲያን መንደር ዘው ብሎ ገብቶ ሲታይ እነርሱኑ መስሎ ቁጭ አለ። ጥበብ ስታዘግን ዓይንም የላትምና ሲራክን የተመለከቱ “አቤት አባመስጠት!” አሏት። ቢሉም እውነታቸውን ነው። “ኧረ ከየት መጥቶ አንዱም አልደረሰኝም” የሚል በበዛበት ከአምስት በላይ ይዞ የሚገማሸረውን ተመልከተው ጥበብን አድሏም! ፍርደገምድል! ቢሏትስ ምን ይገርማል...

ልጅ ተወልዶ ቀዬውን ማስጠራቱ አንድም ጀግንነት ነው። ከሀገሩ ጋር ተዋዶ የሀገሩ ብቻ ሆኖ መኖሩም የወግ ነው። ግንቦት 21 ቀን 1939ዓ.ም ወሎዬው በወሎ ዋድላ ደላንታ፤ በወገል ጤና ታዛ ስር ከእናት ስረባት አስፋው እና ከአባቱም ታደሰ ካሳ ጉዱ ሲራክ ተወለደ። ህጻን ሲራክንም ያየ ለጥበብ ተመኘ። በእድገቱም ምራቅ እንትፍ! እንትፍ! እያደረጉ “የጥበብ ልጅ ጥበብ ታሳድግህ” ሲሉ የመረቁት ይመስል እጎለመሰ ተንበሻበሸባት። ሲራክ ቤተሰቦቹ በክርስትናው ነበሩና ገና ከትንሽነቱ አንስቶ በቤተ እግዚአብሔር ደጅ የጸና ነበር። በዚያም ከሰንበት ዳዊት ደገመ። ድጓና ጾመ፣ ድጓንም ተምሮ ጨረሰ። በአቋቋምም ጎብዞ ቆመ። ሳያበቃም ያሬዳዊ ዜማን ተምሮም አዜመ። ከዚሁ በኋላ ነበር ከትውልድ ቀዬው ተነስቶ የት አለሽ አዲስ አበባ ሲል የተገናኛት። ሲመጣም ቀድሞ የነበረበትን መንፈሳዊ ሕይወቱን አልጣለም። ወደ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ቀርቦ አገልግሎቱን ቀጠለ።

የሊቃውንት ጉባዔ አባል ሆኖ ሲሠራም ነበር። ከልጅነቱ አንስቶ የጥበብ መጀመሪያ በሆነው የጥበብ መንገድ ውስጥ ሲያልፍ ቆይቷል። ከብሩካኑም፣ ከጠቢባኑም ዘንድ ስሙ ተጠራ። ጥበብን ፈለጋት ጥበብንም አገኘ። ያዛትም።

ሲራክና የወዲህኛው የሕይወት ጉልላት በዘመን ተቃጥረው አንድ ቀን በአንድ አጋጣሚ ተገናኙ። ከመጀመሪያው ጀምሮ በልቡ የሚሸተው አንዳች ነገር ሲመላለስበት ነበርና አካባቢውን የደረሰበት መሰለው። በዚያን ጊዜም የምድር ጦር የሙዚቃ ክፍል ያወጣውን ማስታወቂያ ተመለከተ። ማስታወቂያውም በጦር ክፍሉ ውስጥ በሙዚቃ ለመሥራት የሚፈልጉትን አወዳድሮ ስለመቅጠር ነበር። ሲራክም ሁለት ሃሳብ ሆኖ እንደፍጥርጥሩ እያለ ሄዶ በድፍረት ተመዘገበ። ጥበብ ጠርታው በድልም ተወጣውና ክፍሉን ተቀላቀለ። የመጣው በድምጻዊነቱ ቢሆንም ለእርሱ ግን ከዚህም ገዝፎ ውልብ የሚልበት ሌላ የጥበብ አትሮኖስ ይዞ ይታየው ነበር። ሁሌም የሚታየውንና የሚፈልገውን ነገር ዱካ ተከትሎ መሄድ አይሰለቸውምና አሁንም ሾልኮ ገባ። እዚህም ቤት ውስጥ ሲራክ ታደሰ ድምጻዊ ነው ብለው ድምጹን ሲጠባበቁ ድምጹን አጥፍቶ አደፈጠባቸው። የኋላም አንድ አዲስ ነገር ይዞ ወጣ። ድምጻዊነቱን እያደበዘዘ ግጥምና ዜማ ደራሲነቱን በብርሃን አጥለቅልቆ ከፍ አደረገው። የጦር ክፍሉ ምርጡ የግጥምና ዜማ ደራሲ እየሆነም መጣ። ያጥለቀለቀው ብርሃን የጋን ውስጥ መብራት ሳይሆን ከክፍሉ አልፎ እየወጣ በኢትዮጵያ የሙዚቃ መድረክ ላይ በቀይ አበባና ምንጣፍ ተንቆጥቁጦ ወጣ፡፡

ታላቁ ከታላላቆቹ የሙዚቃ ሳተናዎች እግር ስር ብቅ ብሎ ታየ። በሀገራችን ውስጥ የምን ጊዜም ምርጥ ከምንላቸው ድምጻውያን የቀረው ማንም የለም። ሁሉንም አግኝቶ፣ ከሁሉም ጋር ተገናኝቶ፣ ሁሉንም ሰጥቷቸዋል። የደስ ደስ ያላቸውን በርካታ ሙዚቃዎችን ግጥምና ዜማ እየሠራ ከዘገነው አዘግኗቸዋል። የክብር ዶክተር ጥላሁን ገሠሰ አንዱ ነው። “ትንፋሼ ተቀርጾ” እያለ ጥላሁን ገሠሰ ድምጹም ትንፋሹም ተቀርጾ ወጣ። ሁሉም ጆሮውን አቁሞ የማንስ ግጥምና ዜማ ነው ሲል ጠየቀ። የሲራክ ታደሰ ነው ተባለ። “ቀጥል በል ሲራክ ሌላስ ምን አለህ?” አለ ጥላሁንም። ሲራክ ምን ገዶት ወዲህም ወዲያም እያለ ቀጠለ። “ከረምኩዋት” እና “አይ ዘመን” የሚሉ ሌላ ሁለት ሥራዎችንም አከለለት። ወደ ሂሩት በቀለም ዞሮ “ማን ብዬ ልጣራ፣ ሎጋው ቁመናው፣ ዕንቅፋት ሲመታኝ” የሚሉትን ጀባ አላት። ለመልካሙ ተበጀ “የልቤን አዳራሽ፣ ኧረ መላ ምቱ፣ አንቺን ነው እኮ፣ ስቀርብሽ እቱ፣ በቀን አሥር ጊዜ” አለው። ከመልካሙ ተበጀ ጋር በዚህም አላበቃም። እነዚህኑ ጨምሮ ከ15 በላይ የሆኑትን ሸልሞታል። ሲሸልም አስቴር አወቀንም አልረሳ “ሸበል” አስባላት። “በናፍቆት አለንጋ” እና “ሰበቡ” የተሰኙት ሁለት ዜማዎች ደግሞ ለታምራት ሞላ አቀረበለት። ቀጠለና ደግሞ ማህሙድ አህሙድን እየተመለከተ “ዓለም ዓለም ምን ይመስልሻል?” አለ። ምላሹም ይመስላል በቀጣይም ”አልማዝ ዕንቁ መሳይ” ሲል ደገመለት። እዚህ ሁሉ መሀል አለማየሁ እሸቴም አለ። “ፍቅር ፍቅር ነው” በማለት አለማየሁም አቀነቀነና “ምንድነው ፈገግታ”ን ደገመ። የሰማች በዛ ወርቅ አስፋውም መጣች። “መውደድ ሰውነቴ፣ ጓደኛዬ” አላት። የቀረ ማንም አነበረም። ፍቅረአዲስ ነቃጥበብ “ያነቃል፣ አትርሳኝ” ካለች ኋላም የራሰው አነበረም። ምኒልክ ወስናቸው፣ነጻነት መለሰ፣ ጌራ ወርቅ ነቃጥበብ እና ሌሎች ብዙዎችንም በግጥምና ዜማው አስቧቸዋል። በተናጠል ለእያንዳንዱ ሥርቶ ካሰናዳላቸው የግጥምና ዜማ ማዕዶት በተጨማሪም ለምድር ጦር እና ለብሔራዊ ቲያትር የቅብብሎሽ ህብረ ዜማዎችን ለመድረክ አቅርቧል፡፡

“ጉልሽ! ጉልሽ!” እያሉ የተጣሩና የፈለጉት ሁሉ እርሱን ከአንድ የጥበብ ቤት በአንድ ስፍራ ሊያገኙት አልቻሉም። ቲያትር ጋር ሲሉት ሙዚቃ ቤት፣ ራዲዮ ጣቢያ ሲሉ ሲኒማ ቤት ሆነ መገኛው። እርሱን ፈልጎ ለማግኘት የወደደ በየጥበብ ቤቱ ደጃፍ እየዞረ መንከላወስ ግድ አለው። ያ ሁሉ አልበቃ ብሎት ደግሞ ሌላ ስድስተኛም ነገር ሆነ አሉ። እሱስ ለምን ይቅርበት ሲል ወደ ፊልሙ ጥበብም ተቀላቀለ። ሲራክ ፊልም እየሠራ የፊልም አፍቃሪውንም አድናቆት መቀበል ተያያዘው። ድራማውንም አላስተረፈው የራዲዮና የቴሌቪዥን ድራማዎች ላይም እየታየ ድምጹ ተሰማ። ጉልሽ ሁሉ ጥበብሽ!...ከመጀመሪያውም ጀምሮ በትወናው ቲያትርን አብዝቶ ተቀራርቧታል። ስሟን የተሸለመባትን “አምታታው በከተማ”ን ጨምሮ “አሉላ አባ ነጋ፣ ሀሁ በስድስት ወር፣ የአመፃ ልጆች፣ ነጻ ወንጀለኞች፣ መርዛማ ጥላ፣ የአዛውንቶች ክበብ” እና ሌሎች ተወዳጅ ቲያትሮች ላይም ተጫውቶ አስደምሟል። ተወዷል።

ከእለታት በአንዱ ቀን ላይ ነበር... በዚያን ዕለትም የሎሬት ጸጋዬ ገ/ መድህን “እናት ዓለም ጠኑ” ቲያትር ሊታይ ነው። ሲራክ ደግሞ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ወክሎ ይጫወታል። ታዲያ በዘውዱ ሥርዓት አነበረም፤ በደርግ እንጂ። ንጉሡም ከሞቱ ድፍን አንድ ወር ሞልቷል። የዚያን ዕለት ቲያትሩም ይመረቃልና የወቅቱ ጌታ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያምም ከመድረኩ ፊት ጉብ ብለዋል። ቲያትሩ መታየት ጀመረ። ጃንሆይን ወክሎ የሚጫወተው ሲራክም በመልክ፣ በቁመናና በድምጻቸው ሁሉ ቁጭ እሳቸውን ከመምሰሉ አልፎ ሊሆን የቀረው አነበረም። እውነት ይሁን ግነት ባይለይለትም ጃንሆይ መስሏቸው ቆመው እጅ የነሱት ሰዎችም ነበሩ ይላሉ። እናም ቲያትሩ ተጠናቆ በስተመጨረሻ ኮሎኔል መንግሥቱ የእያንዳንዱን አርቲስት እጅ እየጨበጡና በርቱ እያሉ ቸብ ቸብ እያደረጉ ሲራክ አጠገብ ደረሱ። መልከት ካደረጉት በኋላም የምን እጅ ብለው ፊታቸውን እያኮሳተሩ በዚያው ጥለውት ወጡ። መቼም ቲያትር ስለመሆኑ ባያጡትም ሲራክ ግን ደህና አድርጎ በመምሰል ስላሳመናቸው ነበር። ጉዱ ሲራክ ጉዱ ሳይፈላ በዚያው ተገላገለ።

ሲራክ ታደሰ ከወሎ ዋድላ ደላንታ ሲከንፍ በአውቶብሱ አዲስ አበባ ላይ ደርሶ፣ በአዲስ አበባም ገብርኤል ቤተ ክርስቲያንን ተሳልሞና ጸሎት አገልግሎቱን አድርሶ፣ በተማረው ጥበብ ጥበብን ፍለጋ ወጣ። ከምድር ጦር ደጃፍም ፈላጊው ሲራክና ተፈላጊዋ ጥበብ ተገናኙ። ተቃቀፉ። መጨረሻም ተዋደዱ። ብዙ ዓመታትንም በምድር ጦር ቤት ከርሞ ኋላም በብሔራዊ ቲያትር ከተመ። ዓመት ሄደ ዓመታት ተተኩ። እርሱ ዕድሜው እየገፋ ሲያረጅ፤ የያዛት ጥበብ ደግሞ ትኩስ አፍላ ወጣት እየሆነች ትሄድ ነበር። በዚህ የተነሳም ዕድሜውና ጥበቢቷ ግብግብና ሙግት ገጠሙ። ዕድሜው “ይህ ሰው አርጅቶ ሸብቷል። ከእንግዲህ ይበቃዋል! ጡረታ ካልወጣ...” ብሎ ደነፋ። ጥበብም “እርሱ የኔ ነውና አያገባህም። በቃ ተወን! እኔም ያለ እርሱ አይሆንልኝም” ስትል በግድም በውድም አሳመነችው። ሲራክ በወቅቱ በብሔራዊ ቲያትር ቤት ውስጥ በመሥራት ላይ ሳለ ነበር የጡረታ ዕድሜው ከየት ሳይባል መጥቶ ከተፍ ያለው። እናም የቲያትር ቤቱ ኃላፊዎችም ከአንድ ካልተለመደ ውሳኔ ላይ ደረሱ። ከቤቱና ከጥበብ መለየት የለበትም በማለት ጡረታውን 5 ዓመት ወደኋላ አሸሹለት። ጉዱ ሲራክ ሌላ ጉድ አሠራቸው። ምን ዓይነቱ እንቁና የጥበብ ፈርጥ የነበረ ስለመሆኑ የተጨመሩለት እኚህ አምስት ዓመታት ማሳያ ምስክሮች ናቸው፡፡

አንድ ወደፊት አንድ ወደኋላ...ተክሌ ደስታ የሲራክ የቅርብ ወዳጁ ነበር። ያኔ ጉብል ወጣት ሳሉ ሁለቱም ወንድማማቾች አካባቢ ሦስት ክፍሎች ያለው ቤት ተከራይተው ሲራክ ሁለቱን ክፍል ላውንደሪ ቤት አደረጋቸው። ተክሌ ሲያስታውሰው ሲራክ በጊዜው እጅግ ዘናጭና ቆፍጠንጠን ያለ ነበር። ቁመቱ አጭር ብትሆንም ማማርና ማማለሉንም ይችለበታል። ሁሌም እዚያች የቤቱ በራፍ ላይ ቆሞ ይጠባበቃል። የሚጠባበቀውም ከትምህርት ቤት መልስ ሁል ጊዜም በዚያ የምታልፈውን አንዲት ቆንጆ ልጃገረድን ነበር። ባለፈች ቁጥርም ቆሞ ያያታል። እሷም ሰረቅ እያደረገች ታየዋለች። በጥርሶቿ ብልጭታ ፈገግታዋንም ታጎናጽፈውና በህፍረት ፊቷን በደብተር አሊያም በቦርሳዋ እየሸፈነች ትሄዳለች። አልፋው እንደሄደችም እግሮቿን ብርክ እየያዛቸው ይንቀጠቀጡና ይደነቃቀፋሉ። ዛሬም ትመጣለች...ደግሞ አልፋው ትሄዳለች። ይህችን ታሪክም ሲራክ በመልካሙ ተበጀ ውስጥ ዘፈናት።

**“ኧረ መሳ ምቱ ዘመድ ወዳጆቼ**
**አይናፋር ሆኛለሁ አይናፋር አይቼ**
**ሰላምታ አልሰጠኋት አላነጋገርኳት**
**ባይኔ ብቻ እያየሁ አንድ ዓመት ወደድኳት”**

ሲራክ ጻፈ። መልካሙ አዜመ። ሙዚቃውም ተወደ፣ እንደተወደደ ዛሬም ድረስ አለ። አምስትና ሲራክ ተዛምዷቸው ብዙ ይመስላል። ሲራክ ሌላም የራሱ ሕይወት ነበረው። የራሱም ዘመን ነበረው። በሕይወት ዘመኑም የአምስት ልጆች አባት ነበር። ሁለት የሴት አትሮኖሶች፣ ሦስትም የወንድ ላምባዎችን ከፊቱ አስቀመጠ። ሞትም ከበስተጀርባው አፈጠጠ። ይኼኔ ግን ጥበብም የዘለዓለም እረፍትን ተመኘችለት። ተሰናበታት። ሄደ። የህመም ብርክ ያዘው። ከአልጋ ላይ ወደቀ። ብዙ ህክምና ብዙ ጥረትም ተደረገለት። ሞት ግን እንደ ጡረታ አነበረም። አምስት ዓመታትን ቀርቶ አምስት ወር፣ ሳምንት፣ ቀን፣ ደቀቂቃ፣ ሴኮንድም ጠፋና አረፈ። ለሞት ምንም የባከኑ ደቂቃና ሴኮንዶች የሉትም። መስከረም 8 ቀን 2001 ዓ.ም ከወዲህኛው ወደ ወዲያኛው ተጓዘ። 63 ዓመታት አንድ ሞት...ጉዱ ሲራክ ለጉድ ሠርቶ፣ ጉድ አስብሎ፣ በጉድ ቀን ሄደ፡፡



# የጎርጎራ ፕሮጀክት ለሀገር የሀብት ምንጭ መሆን በሚችል መልኩ ተሠርቷል

## - ቱሪስቶች ወደ ስፍራው በመሄድ እየጎበኙት ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ጣናን ተንተርሶ የተሠራው የጎርጎራ ፕሮጀክት ለሀገርና ለአካባቢው ሕዝብ የገቢ ምንጭ መሆን በሚችል መልኩ ተሠርቷል ሲሉ የአማራ ክልል የኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ መንገሻ ፈንታው (ዶ/ር) ገለጹ።

የአማራ ክልል የኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ መንገሻ ፈንታው (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፡- ጣናን ተንተርሶ የተሠራው የጎርጎራ ፕሮጀክት ለአካባቢው ሕዝብና ለሀገር ከፍተኛ የሆነ የሀብት ምንጭ መሆን በሚችል መልኩ ተሠርቷል።

በገበታ ለሀገር ፕሮጀክት ተካተው በሀገሪቱ ከተሠሩ ፕሮጀክቶች የጎርጎራ ፕሮጀክት በጥራቱ፣ በውበቱ፣ በስፋቱ፣ ባሉት ፀጋዎች አንዱ ነው ያሉት ኃላፊው፤ ፕሮጀክቱ ጣናን ተንተርሶ በታሪካዊው የጎርጎራ ቦታ ላይ ተሠርቷል ብለዋል።

ጎርጎራ በጠቅላይ ሚኒስትሩና ከፍተኛ አመራሮች ድጋፍና ክትትል ታክሎበት ለፍጻሜ መብቃቱን ጠቅሰው፤ ፕሮጀክቱ አስደማሚና የዓለም ማኅበረሰብን የሚጋብዝ፣ ታይቶ የማይጠገብ የተፈጥሮ ፀጋ የተሰጠው አካባቢ መሆኑን ገልጸዋል።

በክልሉ በተፈጠረው አንጻራዊ ሠላም የጎርጎራ ፕሮጀክት ለጎብኚዎች ክፍት መሆኑን የገለጹት የቢሮ ኃላፊው፤ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች በቦታው በመሄድ እየጎበኙ መሆኑን ተናግረዋል።

የውጭ ሀገር ጎብኚዎች ወደ ቦታው እንዲመጡ የማስተዋወቅ ሥራ ይሠራል ብለዋል።

የጎርጎራ ፕሮጀክት ከቱሪስት መስሕብነት አኳያ መልከ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው ተናግረዋል።

ክረምት የበርካታ ሀገራት የአየር ሁኔታ ሞቃታማ መሆኑን ተንተርሶ የውጭ ሀገራት ቱሪስቶች ወደ ኢትዮጵያ እንደሚመጡ ጠቅሰው፤ በገበታ ለሀገር ፕሮጀክት ሀገሪቱ ያላትን ውብ የተፈጥሮ ፀጋ በሚያሳይ መልኩ አሳምሮ በመሥራት ለቱሪስት ምቹ ማድረግ መቻሉን ገልጸዋል።

ጎርጎራ ፕሮጀክት በውስጡ በጣና ሐይቅ ላይ የተገነባ አንፊ ቴአትር፣ ሬስቶራንትና ሌሎች አገልግሎቶችንም መያዙን በመግለጽ፤ ሰሜን ኢትዮጵያን የቱሪዝም መዳረሻነትን የሚያጎለብት ሀገራዊ ልማት መሆኑን ተናግረዋል።

ከፀጥታ አኳያ አንጻራዊ ሠላም በአካባቢው መኖሩን በመግለጽ፣ በጫካ ካሉ ወንድሞች ጋር ችግሮችን በውይይት በመፍታት የአካባቢውን ፀጋ እድሎችን መጠቀም እንደሚቻልም ጠቁመዋል።

የውጭና የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ክልሉን እንዲጎበኙ አስተማማኝ ሠላም መምጣት እንዳለበት የገለጹት ኃላፊው፤ በክልሉ የፀጥታው ችግር ሳቢያ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎችና ሆቴሎች ላይ የተገልጋይ ቁጥር ቀንሷል ብለዋል።

ችግሮችን በሠላማዊ መንገድ በመፍታት የቱሪስት ፍሰቱን ወደ ቀድሞ እንቅስቃሴው መመለስ አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰው፤ ቱሪዝምን ጨምሮ ለሁሉን አቀፍ ኢኮኖሚያዊ እድገት ለማምጣት ሠላም አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል።

የተሠሩ ፕሮጀክቶችን ቱሪስት እንዲጎበኛቸው ሠላም ለማስፈን ሁሉም የድርሻው ሊወጣ እንደሚገባ ገልጸው፤ በጎርጎራ ያለውን ውብ የተፈጥሮ ጸጋ አሳምሮ በመስራት ለቱሪስት ምቹ ማድረግ መቻሉን ተናግረዋል።

# “አገልግሎት አሰጣጥን በቴክኖሎጂ በመደገፍ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ወደ ዲጂታላይዜሽን ለመሸጋገር በትብብር መሥራት ይገባል። በተለይ አገልግሎት አሰጣጥን በቴክኖሎጂ በመደገፍ ጊዜና ሀብትን ከብክነት መታደግ ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ካደጉ ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ እያደረገች ያለው ጥረት ማለትም የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት መቋቋሙ፣ አምስት ሚሊዮን ‘ኮደሮች’ መርሐ ግብር ይፋ መሆኑ፣ በፖሊሲ የታገዘ የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ስትራቴጂ መፅደቁ እና ሌሎች በርካታ ሥራዎች መሠራታቸው የሚበረታታ ነው ሲሉ አስታውቀዋል።

የግልና የመንግሥት ተቋማት የዲጂታል ዳታ ክምችትን በአግባቡ በማስቀመጥ፣ ልምድና ተሞክሮ በመለዋወጥ፣ አገልግሎት አሰጣጣቸውንና መረጃ አያያዛቸውን በቴክኖሎጂ በመደገፍ ሀገሪቱ የምታወጣውን የጊዜና የሀብት ብክነት ሊታደጉ ይገባልም ብለዋል።

እያንዳንዱ ተቋማዊ መረጃ ለተተኪው ትውልድ ወሳኝ ግብዓት መሆኑን በመረዳት እያንዳንዷን መረጃ ዲጂታላይዝድ በማድረግና በአግባቡ በመሰነድ ለቀጣዩ ትውልድ መሠረት መጣል ይገባል ሲሉ አመላክተዋል።

ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥና መረጃ አያያዝን ዲጂታላይዝድ ማድረግን እና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሳደግ በእቅዳቸው ውስጥ በማካተት ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት ይጠበቅባቸዋል ነው ያሉት።

ሁሉም ተቋማት ከኋላ ቀር አሠራር በመውጣት በቴክኖሎጂ የታገዘ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ የሚመለከተው ባለድርሻ አካል በፖሊሲ ሊደግፋቸው እንደሚገባም ጨምረው ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ ኢንተርኔት ከማስፋፋት፣ የተማረ የሰው ኃይል ከማፍራትና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ከማሳደግ አንጻር ጥሩ ጅምር ሥራዎች መኖራቸውን ገልጸው፤ በዚህም ሁሉም ሰው መረጃን ጊዜና ቦታ ሳይገድባቸው በፍጥነትና በእኩል ማግኘት የሚችሉበት እድል ተፈጥሯል ሲሉ ተናግረዋል።

የዓለም ሀገራት የቴክኖሎጂ ዘርፍን የመወዳደሪያ መስፈርት አድርገው በትኩረት እየሠሩበት ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ግብርና፣ ጤና፣ ፋይናንስ እና ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎችን ከቴክኖሎጂ ጋር በማዛመድ አገልግሎት አሰጣጣቸውንና መረጃ አያያዛቸውን በማዘመንና በማቀላጠፍ ምርትና አገልግሎታቸውን ማሳደግ ችለዋል ሲሉ አብራርተዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት የመረጃ አያያዝ ቴክኖሎጂን ማሳደግ፣ ብቁ የሰው ኃይል ማፍራት፣ የማሽን ቋንቋ ያልሆኑ ሀገረኛ ቋንቋዎችን ማሽን እንዲያውቃቸው የማድረግ ሥራዎች ትኩረት ከተሰጠባቸው ተግባራት መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

የቴክኖሎጂ አጠቃቀም አቅምን በማሳደግ፣ አሠራርን ለማዘመን፣ ሀብትና ጊዜን ከብክነት ለመታደግ ሁሉም ባለድርሻ አካላት አሠራራቸውንና ፖሊሲያቸውን በደንብ በመፈተሽ ማሻሻል እንደሚኖርባቸው ጠቁመው፤ ኢትዮጵያን በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ካደጉ ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ በቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ፈጠራ ብዙ መሥራት ይገባል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# ዓለም አቀፍ



## አዛውንቶቹ ዘራፊዎች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በጃፓኗ ሆኬዶ በተሰኘችው የወደብ ከተማ ቤቶች እየተሰበሩ ዝርፊያ ይፈጸምባቸዋል።ጥቆማ የደረሰው ፖሊስ የወንጀሎቹን ፈጻሚዎች በቀላሉ ማግኘት አልቻለም ነበር፡፡

ፖሊስ ወንጀሉን ቶሎ እንዳይደርስበት ዋናው ምክንያት ደግሞ ወንጀሉን አዛውንቶች ላይፈጽሙት ይችላሉ በሚል ነበር፡፡

በመጨረሻም ሁነቶችን ለመከታተል የተተከሉ ካሜራዎችን ከተመለከተ በኋላ ዝርፊያውን አንድ አዛውንት ሲፈጽም ይመለከታል፡፡

የአንዱን አዛውንት እንቅስቃሴ ላይ ባደረገው ክትትል የ88፣ 70 እና 69 ዓመት እድሜ ያላቸው ጃፓናውያን አዛውንቶች ተደራጅተው ሲሰርቁ መቆየታቸውን ያረጋግጣል፡፡

እነዚህ አዛውንት ጃፓናውያን አንዱ የሚሰበሩ ቤቶችን በማጥናት ሲሰብር እና ሲሰርቅ፣ አንዱ ደግሞ የተሰረቁ ንብረቶችን በማጓጓዝ ሌላኛው ደግሞ ንብረቶቹን የሚገዛ ደንበኛ አፈላላጊ ሆነው እየሠሩ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

ፖሊስ የአዛውንቶቹን ሙሉ የስርቆት ሰንሰለት ካጠና በኋላ በቁጥጥር ስር ያዋላቸው ሲሆን ወንጀሉን እንደፈጸሙ አምነዋል ተብሏል፡፡

አዛውንቶቹ ስርቆቱን ለምን እንደፈጸሙ ሲጠየቁም ኑሮ ከብዷቸው ሕይወታቸውን ለማቆየት ብለው ወደ ስርቆት እንደገቡ ለፖሊስ ተናግረዋል ሲል ኦዲቲ ሴንትራል ዘግቧል፡፡

የአዛውንት ሕዝብ ብዛት በበዛባት ጃፓን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጡረታ በወጡ አባቶች የሚፈጸሙ ስርቆት ወንጀሎች እየጨመሩ መምጣታቸው ተገልጿል፡፡

በጃፓን በየዓመቱ ከሚወለዱ ሕጻናት ይልቅ ጡረታ የሚወጡ አዛውንቶች ቁጥር ብልጫ አለው የተባለ ሲሆን ሀገሪቱ ዜጎቿ ጋብቻ እንዲመሠርቱ እና ልጆችን እንዲወልዱ የተለያዩ ማበረታቻዎችን ዘርግታለች፡፡

## የሕንዱ ጠቅላይ ሚኒስትር ናሪንድራ ሞዲ በዩክሬን ጉብኝት ሊያደርጉ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የሕንዱ ጠቅላይ ሚኒስትር ናሪንድራ ሞዲ በነሐሴ መጨረሻ ወደ ዩክሬንን እንደሚጎበኙ ተነገረ፡፡

ለሦስተኛ ጊዜ የሥልጣን ዘመን ቃለ መሐላ ከፈጸሙ በኋላ በመጀመሪያ ይፋዊ የውጭ ሀገር ጉብኝታቸው በቅርቡ ሩሲያ የነበሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዩክሬን እና በሩስያ መካከል ጦርነት ከተቀሰቀሰ ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ኬቭ ያቀናሉ።

ሞዲ ፕሬዚዳንት ቮላድሚር ዘለንስኪ ባዘጋጁት የተለያዩ የሠላም ጉባኤዎች ላይ እንዲሳተፉ ጥሪ ቢቀርብላቸውም ሳይታደሙ ቀርተዋል፡፡

ከቭላድሚር ፑቲን ጋር ጥብቅ ወዳጅነት ያላቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሩስያ ላይ ጫና ለማሳደር እና ማዕቀብ ለመጣል በተደረጉ የተመድ እና የሌሎች የባለ ብዙ ወገን ጉባኤዎች ላይ ገለልተኛ ሆነው ዘልቀዋል።

አሜሪካ እና ምዕራባውያን በጦርነቱ ምክንያት ሩስያ ከዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ እንድትገለል እንዲሁም በኢኮኖሚያዋም ላይ ጫና ለመፍጠር ላሰቡት እቅድ ሕንድ እና ቻይና እንቅፋት የሆኑ ይመስላል፡፡

የተለያዩ የአውሮፓ ግዙፍ ኢኮኖሚ ሀገራት መሪዎች ከአንድም ሁለት ጊዜ በዩክሬን ተገኝተው አጋርነታቸውን ሲገልጹ ሞዲ ጦርነቱ ከተጀመረ ጀምሮ አንድም ጊዜ ወደ ስፍራው አላቀኑም፡፡

በቅርቡ በሩስያ የነበራቸውን ጉብኝት ተከትሎ የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ዘለንስኪ በኤክስ ገጻቸው የዓለም ትልቁ ዴሞክራሲ ከዓለም ትልቁ ወንጀለኛ ጋር ሲተቃቀፍ ማየት ያሳፍራል የሚል ጽሑፍ አስፍረው እንደነበር ይታወሳል፡፡

ይህን ተከትሎም በሕንድ የሚገኙት የዩክሬን አምባሳደር በጉዳዩ ላይ ምላሽ እንዲሰጡ በሕንድ መንግሥት ታዘው ነበር፡፡

በሩስያ እና ዩክሬን ጦርነት ተፅዕኖ መፍጠር የሚችሉት ምዕራባውያን ሁለቱን ሀገራት ከማቀራረብ እና ከማደራደር ይልቅ ለዩክሬን ይፋዊ ውግንናቸውን ገልጸው ጦርነቱን መደገፍ መርጠዋል በዚህ መካከል ጦርነቱ ሦስት ዓመቱን ሊደፍን ጥቂት ጊዜያት ቀርተውታል፡፡

የተለያዩ የዓለም አቀፍ ሠላም እና ደኅንነት ተመራማሪዎች የዩክሬን ግጭት ወደ እጅ አዙር ጦርነት ከተቀየረ መሰነባበቱን ያነሳሉ፡፡

ይህን ጦርነት ለመቋጨት የአሜሪካ እና ምዕራባውያን የጦር መሣሪያ ድጋፍ እንዲሁም ተፅዕኖ የሠራ አይመስልም በመሆኑም ግጭቱ ይቆም ዘንድ ወይ እንደ ሕንድ እና ቻይና ያሉ በሩሲያው ፕሬዚዳንት ላይ በጎ ተፅዕኖ ማሳደር የሚችሉ አካላት ወደ ፊት መምጣት ይኖርባቸዋል ካልሆነም ደግሞ አንዱ ሀገር እስኪሸነፍ ድረስ ጦርነቱ ይቀጥላል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የሀንጋሪው ጠቅላይ ሚኒስትር ቪክተር ኦርባን ሁለቱን ሀገራትን ለማቀራረብ አድርገውት የነበረው የዲፕሎማሲ ጉዞም ከአውሮፓ ኅብረት ከፍተኛ ተቃውሞ ገጥሞታል፡፡

ሲኤንኤን ላይ ትንታኔ የሚጽፈው ሳይመን ማካርቲ ምዕራቡ የተሳነውን አልያም ችላ ያለውን የማሸማገል ሥራ ቻይና ተሳክቶላታል ሲል ጽፏል፡፡

በዚህ ሳምንት የፍልስጤም ተቀናቃኞቹን ፋታህ እና ሃማስ አብረው እንዲሠሩ እና ከግጭት እንዲወጡ ያስማማችው ቤጂንግ ከዩክሬኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዲሚተሮ ኮሊባ ጋር ተወያይታለች፡፡

በቻይና ከፍተኛ የዩክሬን ባለሥልጣን ከጦርነቱ በኋላ ጉብኝት ሲያደርግ ይህም ለመጀመሪያ ጊዜ ነው፡፡

ቤጂንግ እና ኒውደልሂ ሩስያ እና ዩክሬንን ለማደራደር አብረው ቢሠሩ ሁነኛ ውጤት ላይ ሊደርሱ እንደሚችል ይገመታል ለዚህም የአሁኑ የሕንዱ ጠቅላይ ሚኒስትር ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ዩክሬን የሚያደርጉት ጉብኝት ወሳኝነቱ ከፍተኛ ነው ተብሏል፡፡

# ስፖርት





## ከድል በላይ የደመቀው ታሪክ ሲታወስ

ብርሃን ፈይሳ

ክስተቱ ከተፈጠረ ሁለት አስር ዓመታትን ቢያስቆጥርም ዛሬም ድረስ ደምን እንዳሞቀ ቀጥሏል። በአረንጓዴ መለያ የቀረቡት ሦስቱ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች መም ላይ ያሳዩት የሃገርና የወገን ፍቅር በእርግጥም በስታዲየም የታደመውን የአትሌቲክስ ቤተሰብ ቆሞ እንዲያጨበጭብ አድርጓል። ‹‹ታሪክ ተሠራ›› በሚል ቃል በተደመደመው ሩጫ መዋደድ፣ መከባበር እና አብሮነት በግልጽ ታይተዋል። እአአ በ2004 የሆነው ይኸው ክስተት ዓመታትን ተሻግሮ ዛሬም ድረስ የሚወሳ ለወጣት አትሌቶችም ተምሳሌት ሲሆን የሚኖር ነው።

የኦሊምፒክ ጨዋታዎች መነሻ የሆነችው አቴንስ ባሰናዳችው በዚህ ኦሊምፒክ ላይ ኃይሌ ገብረስላሴ፣ ቀነኒሳ በቀለ እና ስለሺ ስህን ኢትዮጵያን በ10ሺ ሜትር ሊወክሉ ተሰለፈዋል። ከሩጫው መጀመር አስቀድሞ የሕመም ስሜት በእግሩ ላይ የነበረበት ታላቁ አትሌት ኃይሌ በዓለም ሻምፒዮናው እንደተመዘገበው ከቡድን አጋሮቹ ጋር በመሆን ከወርቅ እስከ ነሐስ ያለውን ሜዳሊያ ወደ ሃገሩ ለመመለስም ነበር በሩጫው የተካፈለው። ርቀቱ እየጨመረ ሲመጣም አምስት አትሌቶች ብቻቸውን ቢቀሩም እንደታሰበው ግን ሶስቱም ኢትዮጵያውያን ወደፊት መውጣት አልቻሉም።

የመጨረሻዎቹ የርቀቱ ዙሮች ላይ ቀድሞ በሚታወቅበት ሁኔታ መውጣት አቅቶት ከመሪዎቹ ወጣት አትሌቶች ቀነኒሳ እና ስለሺ የተነጠለውን ኃይሌን እንዲመጣ ጠበቁ። በሩጫቸው መካከል ዘወር እያሉ በተደጋጋሚ አሯሯጡን ሲቃኙ ቆዩ፤ የእሱ ሃሳብ ግን የሃገርና የሕዝብን አደራን ተቀብለዋልና ሁለቱ እንዲወጡ ነበር። በመጨረሻም ወሰኑ፤ ተከታትለውም ተወነጨፉ። በውድድሩ ማብቂያም ኢትዮጵያ የወርቅ እና የብር ሜዳሊያ እንዲሁም በኃይሌ ዲፕሎማን አስመዘገበች።



**የአቴንስ ኦሊምፒክ የ10ሺ ሜትር ወንዶች ታሪክ ሁሌም የማይረሳ ነው፣**

ፈጣኑ ቀነኒሳ የገባበት 27 ደቂቃ ከ05 ሰከንድ ከ10 ማይክሮ ሰከንድ የሆነ ሰዓትም የርቀቱ የኦሊምፒክ ክብረወሰን ሆኖ ተመዘገበ።

ልብ የሚነካውን የሃገርና የወገን ፍቅር የተመለከቱት በስታዲየሙ የሚገኙ ታዳሚዎችም በአድናቆት ቆመው ለማጨብጨብ ተገደዱ። የወጣቱ አትሌት ድንቅ አሯሯጥም ‹‹ቀነኒሳ አንበሳ›› ተብሎ እንዲዘፈንለት አደረገ። ይህ ሁኔታ ዓመታትን ቢያስቆጥርም እነሆ ዛሬም ድረስ ግን ከአትሌቲክስ ቤተሰቡ ሕሊና ሳይፋቅ እንደታተመ ይኖራል። የያኔው ወጣት አትሌት የመጀመሪያ የኦሊምፒክ ተሳትፎ ይህን መሰል ታሪክ የጻፈው አትሌት ቀነኒሳ በቀለ፤ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ችሎታውን ለዓለም የገለጠበትም ነበር።

ኃይሌ የመም ሩጫዎች ማምሻው ላይ በነበረበት ወቅት የተገኘው የ21 ዓመቱ ቀነኒሳ በአቴንስ ምድር ካንጸባረቁ እጅግ ድንቅና ጀግና አትሌቶች ተርታም ሊሰለፍ ችሏል። በ21ኛው ክፍለ ዘመን ከታዩ ምርጥ የዓለም አትሌቶች መካከል አንዱ የሆነው ቀነኒሳ ከ20 ዓመታት በኋላም እነሆ ሃገሩን በዚህ የውድድር መድረክ ከመወከል ወደኋላ አላለም። በ3 የኦሊምፒክ ተሳትፎ ባስቆጠራቸው 4 የኦሊምፒክ ሜዳሊያዎች ኢትዮጵያውያንን አስፈንጥዟል።

ቀነኒሳ በ10ሺ ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ ባጠለቀ የ5 ቀናት ልዩነት ሁለተኛው ውድድር ላይ ተሰለፈ። እንደ ታላላቆቹ አትሌቶች ሻምበል ምሩፅ ይፍጠር እና ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ በሁለቱም ርቀቶች የወርቅ ሜዳሊያዎችን ያስመዘግባል በሚል ይጠበቅ ነበር። ይሁንና በ5ሺ ሜትር ድንገት በተፈጠረ የቴክኒክ ስህተት የብር ሜዳሊያ ለማጥለቅ በቃ።

## ቀነኒሳ በቀለ

እንደ ታላላቆቹ አትሌቶች ሻምበል ምሩጽ ይፍጠር እና ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ በሁለቱም ርቀቶች የወርቅ ሜዳሊያዎችን ያስመዘግባል በሚል ይጠበቅ ነበር። ይሁንና በ5ሺ ሜትር ድንገት በተፈጠረ የቴክኒክ ስህተት የብር ሜዳሊያ ለማጥለቅ በቃ።

እአአ 2003 ፓሪስ ላይ ተካሂዶ በነበረው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና በ10ሺ ሜትር የወርቅ እንዲሁም በ5ሺ ሜትር የነሐስ ሜዳሊያ በማጥለቅ የስፖርት ቤተሰቡን ያስፈነጠዘው አትሌት ቀጣዩን ዓመትም በድል ታጅቦ ነበር የጀመረው። በዓለም ሃገር አቋራጭ ሻምፒዮና 2 የወርቅ ሜዳሊያዎችን በማግኘት የውድድር ዓመቱን አሃዱ ካለ በኋላ፤ በ5ሺ ሜትር ደግሞ የቤት ውስጥና ከቤት ውጪ የዓለም ክብረወሰኖችን በ9 ቀናት ልዩነት በመሰባበር ሳይጠበቅ ድልን በድል ላይ ደራርቦ ለማግኘት በቃ። የወጣቱ አትሌት ይህ አስደናቂ ብቃትም በዚያው ዓመት በአቴንሷ ፓሪስ ለሚካሄደው ኦሊምፒክ ኢትዮጵያን ለመወከል አበቃው፡፡

4 የኦሊምፒክ ሜዳሊያዎችን ያጠለቀው፣

እአአ በ2012 የለንደን ኦሊምፒክ ላይ በ10ሺ ሜትር አራተኛ ደረጃን ይዞ ካጠናቀቀ በኋላ በተካሄዱ ኦሊምፒኮች ሳይታይ ቆይቷል። በእርግጥ ከዚያ በኋላ ያሉትን ዓመታት ያሳለፈው ከታወቀበት የመም ሩጫ ወጥቶ በማራቶን ሯጭነት ነው። ከአስደሳች ብቃቱ እኩል አሳዛኝ ጉዳቶችን በተደጋጋሚ ማስተናገዱ ደግሞ የአትሌቲክስ ቤተሰቡ ለማየት የሚጓጓለትን ምርጥ አሯሯጥ እንዳይመለከት እንቅፋት ሲሆነው ነበር፡፡